# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 170 የካቲት 20 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

የለውጥ ትውልድ ፕሮጀክት በስምንት ዓመታት ተግባራዊ ይደረጋል

## 20 ሚሊዮን ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት ይፋ ተደረገ

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- 20 ሚሊዮን ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክትን የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና የብሬክስሩ ትሬዲንግ ይፋ አደረጉ።

ሚኒስቴሩ ከብሬክስሩ ትሬዲንግ በለውጥ ትውልድ ፕሮጀክት በጋራ ለመሥራት ትናንት ተፈራርመዋል፡፡

የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ የለውጥ ትውልድ ፕሮጀክት በስምንት ዓመታት 20 ሚሊዮን ወጣቶችን አሰልጥኖ ለማብቃት ያለመና በትግበራ ሂደቱ ለ10 ሺህ አሰልጣኞች ሥልጠና የሚሰጥበትም ይሆናል።

የወጣቶችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የልቦና ውቅር ላይ አጠንክሮ መሥራት ቁልፍ ተግባር ሊሆን ይገባል ያሉት ሚኒስትሯ፤ ለሀገሪቱ የልማትና የለውጥ እንቅስቃሴ ወጣቶችን በመልካም ስብዕና የታነጹና ኃላፊነት እንዲሰማቸው ማድረግ እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

መንግሥት የወጣቶችን ሁሉን አቀፍ ተሳትፎና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ እየሠራ መሆኑን የገለጹት

20 ሚሊዮን ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

## ዜጎች በሀገር ግንባታና በሰላም ጉዳዮች ትብብር እንዲያደርጉ ጥሪ ቀረበ

አመለወርቅ ከበደ

አዲስ አበባ፡- ዜጎች በሀገር ግንባታና በሰላም ጉዳዮች ላይ ትብብር ሊያደርጉ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ የሃይማኖት አባቶች ጥሪ አቀረቡ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ሰላምና ጸጥታ አስተዳደር ቢሮና የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ በጋራ ባዘጋጁት የውይይት መድረክ ትናንት ተካሂዷል፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የለሚ ኩራና ቦሌ ክፍላተ ከተማ የካህናት ክፍል ዋና ኃላፊ አባ ገብርኤል ወልደዮሐንስ በወቅቱ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ምዕመናኑ ከሃይማኖት አባቶች ስለሰላምና ፍቅር የሚነገረውን ትምህርት በመቀበል በመደበኛው ሕይወቱ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

የሃይማኖት አባቶች ለሰላምና ለሀገር ግንባታ ዕድገት ትልቅ ሚና እንዳላቸው የተናገሩት አባ ገብርኤል፤ አባቶች በትምህርት ወቅትም ሆነ መንፈሳዊ ልጆቻቸውን በሚያማክሩበት ወቅት ስለሰላምና ልማት የሚያስተላልፉት ምክር ተግባራዊ መሆኑንም መከታተል አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

ዜጎች በሀገር... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



አቶ ግዛው ተክሌ

## ሀገራዊ የሸማቾች መብት ጥበቃ ማኅበር ቦርድ ተመሠረተ

ገጽ 8

## ስሶማሊያ ህልውና የተዋደቀችው ኢትዮጵያ ወይስ የዐረብ ሊግ?

ተስፋ ፈሩ

ዜና ትንታኔ

የዐረብ ሊግ ኢትዮጵያና ሶማሌ ላንድ በቅርቡ የተፈራረሙትን የባሕር በር ስምምነት በጠንካራ ቃላት ማውገዙ ይታወሳል፡፡ ኢትዮጵያ በበኩሏ የውስጥ ጉዳዬ እና ሉዓላዊነቴ ላይ ጣልቃ የመግባት ሙከራ ነው ስትል የሊጉን መግለጫ በጥብቅ ተቃውማዋለች፡፡

ኢትዮጵያ የሶማሊያን ግዛት በኃይል እንድትወስድ አንፈቅድም እስከማለት በደረሱት የግብጽ መሪዎች እንደሚሾፈር የሚነገረው የዐረብ ሊግ፣ ኢትዮጵያ ላይ መሰል ለአንድ ወገን ያዘነበሉ አቋሞችን በመውሰድ ይታወቃል፡፡ የሶማሊያ ህልውና እንዲረጋገጥ የሕይወት መስዋዕትነት ጭምር የከፈለችው ኢትዮጵያ እንጂ የዐረብ ሊግ አይደለም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ሊጉ ኢትዮጵያ ላይ ኢፍትሐዊ አቋም የሚያራምድበት ምክንያት ምንድን ነው ?

ስሶማሊያ ህልውና... ወደ ገጽ 8 ዞሯል



ረ/ ፕሮፌሰር አደም ካሚል



ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳና







# ተቋሙ በግማሽ ዓመቱ 23 ነጥብ 46 ቢሊዮን ብር ገቢ አገኘ

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በ2016 በጀት ግማሽ ዓመት 23 ነጥብ 46 ቢሊዮን ብር ገቢ ማግኘቱን የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አስታወቀ፡፡

የተቋሙ የኮርፖሬት ኮሙኒኬሽን መምሪያ ኃላፊ ደምሰው በንቲ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመርከብ አገልግሎት፣ በጭነት አስተላላፊነት፣ በወደብና ተርሚናል አገልግሎት እንዲሁም በኮርፖሬት አገልግሎት ዘርፍ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል፡፡

በበጀት ዓመቱ የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት 17 ነጥብ 23 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ፤ 23 ነጥብ 46 ቢሊዮን ብር ገቢ መገኘቱን ጠቁመው፤ ከታክስ በፊት ሦስት ነጥብ 26 ቢሊዮን ብር ትርፍ ማግኘቱን አብራርተዋል፡፡

በግማሽ ዓመቱ የድርጅቱን መርከቦችና የኪራይ መርከቦችን በመጠቀም አንድ ሚሊዮን 886 ሺ 399 ቶን ዕቃ ለማጓጓዝ ታቅዶ ሁለት ሚሊዮን 214 ሺ 156 ቶን የተለያዩ ዕቃዎችን ማጓጓዝ እንደተቻለ አስረድተዋል።

የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የገቢና ወጪ ኮንቴይነር ፍሰት 197 ሺ 699 ኮንቴይነር ለማጓግዝ ታቅዶ 204 ሺ 358 ኮንቴነር ማስተናገድ ተችሏል ብለዋል፡፡

በግማሽ ዓመቱ ቀደም ባሉት ዓመታት ተጀምረው መጓተት የታየባቸው ፕሮጀክቶችን በመገምገም አፈጻጸማቸውን ለማሻሻል የክትትል ሥራ መሠራቱን አመላክተው፤ በግንባታ ሂደት ላይ የነበሩ 14 የካፒታል ፕሮጀክቶች በማጠናቀቅ ርክክብ መድረጉን አቶ ደምሰው አስታውቀዋል።

አቶ ደምሰው እንዳመላከቱት፤ በዚህም መጓተት በታየባቸው 10 ፕሮጀክቶች በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ከነበሩበት 52 ነጥብ ስምንት በመቶ አፈጻጸም ወደ 73 ነጥብ ሁለት በመቶ ማምጣት መቻሉን ገልጸዋል፡፡

በቃሊቲና ሞጆ ወደብና ተርሚናል ቅርንጫፎች እንዲሁም በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች እየተከናወኑ የሚገኙ የፕሮጀክት ሥራዎች ውጤታማ መሆናቸውንም አቶ ደምሰው ጠቁመዋል።

በአጠቃላይ ድርጅቱ የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት ከመደገፍና አትራፊነቱን ጠብቆ ከመቀጠል በተጨማሪ ወጪ ንግድን ለማበረታታት መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት በማኑፋክቸሪንግና በወጪ ንግድ ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ድጋፎችን እያቀረበ መሆኑን አስረድተዋል።

በሚሰጡ ድጋፎች መሠረት በወጪ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ባለሀብቶች ለምርት ግብዓትነት ለሚያስገቧቸው ጥሬ ዕቃዎች፣ ከየብስ ትራንስፖርት የትርፍ ህዳግ እንዲሁም ከባሕር ትራንስፖርት የትርፍ ህዳግ የዋጋ ቅናሽ እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

የኢትዮጵያ የባሕር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ የአፈር ማዳበሪያ፣ የቁም እንስሳት፣ የኮንስትራክሽን ግብዓቶችን የተለያዩ የወጪና ገቢ ምርቶችን በባሕር ከማጓጓዝ በተጨማሪ በሀገር ውስጥ መርከበኞችን በማሰልጠን ላይ የሚገኝ ተቋም ነው።



ወይዘሮ ሽኩሪያ መሐመድ



ሳሙኤል እሸቱ



ጥሩወርቅ ኃይሌ

# «የዓድዋ ሙዚየም ሁሉም ኢትዮጵያዊ የድሉ ባለቤት መሆኑን በገሃድ ያሳየ ነው»

## - ጎብኚዎች

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ሁሉም ኢትዮጵያዊ የድሉ ባለቤት መሆኑን በገሃድ ያሳየ የታሪክ አምድ ነው ሲሉ የሙዚየሙ ጎብኚዎች ገለጹ፡፡

ሙዚየሙን ሲጎበኙ ያገኘናቸው ወይዘሮ ሽኩሪያ መሐመድ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ዘመኑን የሚመጥን ግንባታና ትውልድ ስለታሪኩ ያለውን ግንዛቤ በማሳደግ ረገድ ፋይዳው የጎላ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ቅርስ ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ለኢፕድ ሰጥተዋል።

ሙዚየሙ ውበትን ብቻ ሳይሆን ታሪክን ይዞ የተሠራ ፕሮጀክት ነው ያሉት ጎብኚዋ፤ ፕሮጀክቱ በድሉ ላይ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ጀግኖች ዕውቅና የሰጠና የድል ባለቤትነትም የሁሉም የሀገሪቷ ሕዝቦች መሆኑን ያመላከተ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

አዲስ አበባ ፒያሳ ተወልደው ያደጉበት አካባቢ ቢሆንም እንደዚህ ዓይነት ትልቅ ፕሮጀክት በአካባቢው አይተው እንደማያውቁ ጠቁመው፤ ከሙዚየሙ ግንባታ በኋላ ታሪክን የሚመጥን ለትውልድ መተላለፍ የሚችል ቅርስ መገንባት መቻሉን አስረድተዋል።

በድሉ ወቅት የነበሩ መሣሪያዎችን ጭምር የያዙና ጦርነቱ በተግባር ምን ነበር የሚለውን ማሳየት የሚችል ሙዚየም ነው ያሉት ጎብኚዋ፤ በሙዚየሙ ውስጥ ያየሁት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የተዋደቁበትን የዓድዋ ድል በሚመጥነው መልኩ መቅረቡን ነው ብለዋል።

ወይዘሮ ሹክሪያ እንዳስታወቁት፤ የሙዚየሙ ውጫዊ ውበት ለከተማዋ መልካም ገጽታ የራሱን በጎ አስተዋፅኦ ማበርከት የሚችልና ታሪክን በተሻለ መንገድ ለመዘከር የሚረዳ ነው።

ሌላኛው ጎብኚ ወጣት ሳሙኤል እሸቱ በበኩሉ፤ መላው ኢትዮጵያውያን ከጫፍ እስከ ጫፍ ዘርና ጾታ ሳይለዩ ዘምተው ሀገራቸውን ለድል ያበቁበትን የዓድዋ ታሪክ ይበልጥ ዕውቅና እንዲያገኝ የሙዚየሙ ግንባታ ፋይዳው የጎላ ነው ብሏል።

የሙዚየሙ መገንባት የኢትዮጵያ ጦር ዘመናዊውን የጣልያን ወራሪን መርታት የቻለው በሁሉም ኢትዮጵያውያን ደምና አጥንት መሆኑን ጥበብ በተሞላበት መንገድ ማሳየት ችሏል ሲል ተናግሯል።

የሙዚየሙ ግንባታም ዛሬ ላይ የጀግኖቹን ተጋድሎ ማስታወስ የሚችልና የአሁኑ ትውልድም ታሪክን በመልካም እንዲደግም የሚያበረታታ መሆኑን ገልጿል።

የፕሮጀክቱ ግንባታው ደስ የሚያሰኝና ከዚህ ቀደም የቆሻሻ መጣያ የነበረውን ቦታ ወደመስህብነት የቀየረ ጥሩ ፕሮጀክት ነው ብሏል፡፡

ሳሙኤል የሙዚየሙ ግንባታ እንችላለን የሚል መንፈስ የፈጠረና ምን ዓይነት ደማቅ ታሪክ መፍጠር እችላለሁ ብሎ ለራስ የቤት ሥራ የሚያሰጥ ግንባታ ነው ሲል አስተያየቱን ሰጥቷል።

በሀገር ውስጥና በውጭ የሚገኘው ወጣት ሁሉ ሊጎበኘው የሚገባ የዘመኑ መስህብ መሆኑን ሳሙኤል ጠቅሷል፡፡

ሌላኛዋ ጎብኚ ጥሩወርቅ ኃይሌ በበኩሏ፤ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም ከዚህ ቀደም ስማቸው እምብዛም ያልተነሱና ትውልድም ሊያውቃቸው የሚገቡ ጀግኖችን በሚመጥናቸው መልኩ ማውሳት የተቻለበት መሆኑን ተናግራለች።

ለድል መሠረት የጋራ አንድነት ወሳኝ መሆኑን ያነሳችው ጥሩወርቅ፤ የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየም የኢትዮጵያ ድል ብቻ ሳይሆን ጥቁር ነጭን ማሸነፍ ይችላል የሚለውን አስተሳሰብ ለአፍሪካውያን ማጋባት የቻለ በመሆኑ ይበልጥ መዘከር እንደሚገባ አመላክታለች።

አዲስ አበባ ላይ እንደዚህ ዓይነት ታሪክን የሚዘክር ሙዚየም መገንባቱ የትናንትናን አኩሪ ድል ለመዘከርና ዓድዋን በቀጣይ ትውልድ አዕምሮ ሰርጾ እንዲቆይ ለማድረግ ይርዳል ስትል ገልጻለች።

የዓድዋ ድል መታሰቢያ ሙዚየምን በማየት ዓድዋን ለትውልድ ማስተላለፍ ይቻላል ያለችው ጥሩወርቅ፤ ልንናገረው የምንችል ትልቅ ታሪክ ያለን ሕዝቦች ነንና ታሪካችንን ስናውቅ ማንነታችንን ማወቅ እንደምንችል ተገንዝበ መስህቦቹን እያስፋፉ መሄድ ይገባል ብላለች፡፡

# ኢፕድ የሥልጠና ማዕከሉን ወደ ኮሌጅ ለማሳደግ አቅዷል

## - 24ተኛ ዙር ሥልጠና ተጠናቀቀ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሥልጠና ማዕከሉን ወደ ኮሌጅ ለማሳደግ ማቀዱን አስታወቀ። የሥልጠና ማዕከሉ «በፎቶና ቪዲዮ ኤዲቲንግ እንዲሁም በዲዛይን» ለስምንት ተቋማት የሚዲያና የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች ሲሠጥ የነበረውን ሥልጠና ትናንት ተጠናቋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ወንድም ተክሉ ለሠልጣኞች ሰርተፍኬት በሰጡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ 84 ዓመታትን ያስቆጠረው ኢፕድ መረጃዎችን ለሕዝብ ተደራሽ ከማድረግ ባሻገር በዘርፉ ያካበተውን ልምድ ለማጋራት የሥልጠና ማዕከል ከፍቶ እያገለገለ ይገኛል።

ኢፕድ በሥልጠና ማዕከሉ የቴክኒክና የጽሑፍ ሥልጠና፣ ተቋማዊ ክህሎትና አሠራርን የሚያሳድጉ እንዲሁም የተለያዩ ሥልጠናዎችን እየሰጠ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ ወደፊት የሥልጠና ማዕከሉን ኮሌጅ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑንና ለኮሌጁ የሚሆን ሕንፃ የማዘጋጀት ሥራም ተጀምሯል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሥልጠናና አቅም ግንባታ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ እንግዳ መኮንን በበኩላቸው፤ የኢፕድ ሥልጠና ማዕከል በ23 ዙሮች የፌዴራልና የክልል ተቋማትን እንዲሁም የሌሎች ተቋማትን ሠራተኞችና አመራሮች በተለያዩ የሥልጠና ፕሮግራሞች ማሰልጠኑን አስታውሰዋል።

በአሁኑ ወቅት ሥልጠናቸውን ያጠናቀቁት የሥልጠና ማዕከሉ 24 ዙር ሰልጣኞች ሲሆኑ፤ የሥልጠናው ዓይነት «የፎቶና ቪዲዮ ኤዲቲንግ እንዲሁም የዲዛይን» ክህሎትና እውቀት ላይ ያተኮረ መሆኑን ገልፀዋል።



የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር የኮሙኒኬሽን ባለሙያ ዲና ሽፈራው በበኩሏ፤ በኢፕድ ሥልጠና ማዕከል ስትሰለጥን የመጀመሪያዋ እንደሆነና ተቋሙ የሥልጠና ማዕከል እንዳለው እንደማታውቅ ገልፃለች።

ሥልጠናውን ለ10 የሥራ ቀናት እንደተከታተለችና ከሥልጠናው ጥሩ እውቀትና ክህሎት እንዳገኘች የገለጸችው ዲና፤ የሥልጠናው የአሰጣጥ ሂደት፣ የአሠልጣኞች የፈጠራ ችሎታ እና የሥልጠናው ይዘት እርስ በእርስ የተጣጣመ ነው። ይህም የሠራተኞችን ችሎታና አቅም ያሳድጋል ስትል ሃሳቧን ሰጥታለች።

ተቋማ ከኢፕድ ጋር በመተባበር ተጨማሪ ሥልጠናዎችን ለሠራተኞች እንዲያዘጋጅ እንደምትፈልግና በሥልጠናው ደስተኛ መሆኗን ተናግራለች።

የውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት የኮሙኒኬሽን ባለሙያ አቶ መልካሙ ማሞ በበኩሉ፤ በኢፕድ ሥልጠና ማዕከል ለ10 የሥራ ቀናት ሲሰጥ የነበረው ሥልጠና በዘርፉ ዕውቀትና ልምድ ባላቸው አሠልጣኞች የተሰጠ በመሆኑ ሥራውን ለማሳደግ እንደሚያግዘው አስረድቷል።

በፎቶና ቪዲዮ ኤዲቲንግ እንዲሁም በዲዛይን ዙሪያ መሠረታዊ ዕውቀት እንደነበረውና ከሥልጠናው ያገኘውን ክህሎትና ለተቋሙ ውጤታማነት እንደሚያግዘው ተናግሯል።

ሥልጠናው ከሰባት ተቋማት ለተውጣጡ 23 ሠልጣኞች የተሰጠ ሲሆን፤ ሠልጣኞቹ ከውጭ ጉዳይ ኢንስቲትዩት፣ ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ቢሮ፣ ከኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር፣ ከአዲስ አበባ ሴቶች ሕፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ፣ ከብሔራዊ ሎተሪ አስተዳደር ፣ ከብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት እና ከስፔስ ሳይንስና ጂኦስፓሻል ኢንስቲትዩት የተውጣጡ የኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች ናቸው።

# ስትራቴጂው የኢትዮጵያን ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ለማፋጠን ይረዳል

**ተስፋ ፈሩ**

አዲስ አበባ፡- «ኤሌክትሮኒክ መንግሥት ስትራቴጂ» የኢትዮጵያን ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ለማፋጠን እንደሚረዳ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አስታወቀ።

በቀጣዮቹ ስድስት ወራት 15 በመቶ ያህሉን የመንግሥት አገልግሎቶች ዲጂታላይዝድ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ሚኒስቴሩ ገልጿል።

የመጀመሪያው ‹‹የዲጂታል ኢትዮጵያ ሳምንት›› ከሰኞ የካቲት 18 ጀምሮ እስከ የካቲት 22 ቀን 2016 ዓ.ም «የጋራ ጥረታችን ለዲጂታል ኢትዮጵያችን» በሚል መሪ ሃሳብ በተለያዩ ዝግጅቶች እየተከበረ ይገኛል። በትናንት ዕለትም የኤሌክትሮኒክ መንግሥት ስትራቴጂ ዎርክሾፕ ተካሂዷል።

የኤሌክትሮኒክ መንግሥት ስትራቴጂ ዎርክሾፕን ያስጀመሩት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር)፤ ስትራቴጂው የመንግሥትን አገልግሎት በዲጂታል የታገዘ እንዲሆን በማድረግ ዜጎች ባሉበት ሆነው የመንግሥትን አገልግሎቶች በቀላሉ እንዲያገኙ እንደሚያስችል ጠቁመው፤ የወረቀት አልባ አገልግሎት አሰጣጥ አቅምን ለማጎልበት ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝም ተናግረዋል።

በቀጣዮቹ ስድስት ወራት 15 በመቶ ያህሉን የመንግሥት አገልግሎቶች ዲጂታላይዝድ ለማድረግ ዕቅድ ተይዞ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

የዲጂታል ተጠቃሚነትን በማስፋት በ2025 ሁሉም የመንግሥት ተቋማት አገልግሎትን በቴክኖሎጂ ሥርዓት በማሳለጥ የዜጎችን ተጠቃሚነት እንዲያሳድጉ እየተሠራ እንደሚገኝ የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ ኤሌክትሮኒክ መንግሥት ስትራቴጂ የኢትዮጵያን ዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ያፋጥናል፤ ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂን ለማሳካት እና የሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያውን ለማቀላጠፍ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ብለዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ይሽሩን አለማየሁ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ዲጂታል ኢትዮጵያን የመፍጠሩ ጉዞ በቴሌኮም የመሠረተ ልማት ግንባታ፣ በሲስተሞች ልማት፣ በአስቻይ ምህዳር ፈጠራ እና በሰው ሀብት ልማት ረገድ ትርጉም ያላቸው ውጤቶች መመዝገባቸውን አመላክተዋል። ከ526 በላይ የሆኑ የመንግሥት አገልግሎቶችን በኤሌክትሮኒክ አግባብ ለዜጎች ተደራሽ ማድረግ መቻሉንም ተናግረዋል።

በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ ላለፉት 27 አመታት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽንን ጨምሮ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ከቴክኒክ ሥራ ጀምሮ እስከ አማካሪነት የሠሩት ሊሻን አዳም (ዶ/ር) ፤ ኤሌክትሮኒክ የመንግሥት አገልግሎት የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የመንግሥት አገልግሎቶችን በቀጥታ ባሉበት ለዜጎች፤ ለንግድ ተቋማትና ሌሎችም ተገልጋዮች ተደራሽ ማድረግ የሚያስችል ነው ብለዋል።

ስትራቴጂው በመንግሥት እና በሌሎች በሚመለከታቸው አካላት መካከል ፈጣንና አስተማማኝ የዳታ እና የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር እንደሚያስችል አመላክተው፤ ተቋማት የውስጥ ሥራቸውን በቴክኖሎጂ አስደግፈው በሚገባ እንዲያከናወኑ ማድረግን ያካትታል ብለዋል።



**በለጠ ሞላ (ዶ/ር)**

የኢትዮጵያን የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ሥራዎች ለማኅበረሰቡ ለማስተዋወቅ ብሎም ዜጎች የዲጂታል ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ግንዛቤ ለመፍጠር የተሰናዳው ‹‹የዲጂታል ኢትዮጵያ ሳምንት›› በቀሪዎቹ ቀናት የሳይንስ፤ የቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ፖሊሲ፣ ወረዳ ኔት፣ ኢ-ኮሜርስ ስትራቴጂ፣ የግል ዳታ ጥበቃ፣ የኤሌክትሮኒክ መንግሥት ስትራቴጂ፣ የመንግሥት የኢንተርፕራይዝ አርክቴክቸር፣ የኤሌክትሮኒክ ትራንዛክሽን አዋጅ፣ የብሔራዊ ዳታ ማዕከል፣ የዳታ አስተዳደር፣ እና ሌሎችም ቁልፍ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ምክክሮች ይካሄዳሉ።

የዲጂታል አጠቃቀምን ከማሳደግ ባለፈ ብልሹ አሠራርን ለማስወገድና የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ለማስተካከል ያግዛል የተባለው ኤሌክትሮኒክ የመንግሥት ስትራቴጂ ጥናትና ትግበራ በይፋ ከተጀመረ አንድ አመት አስቆጥሯል።



# በጤናው ዘርፍ የማኅበራዊና ባህሪ ለውጥ የማምጣት ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- በሦስተኛው ሀገር አቀፍ የማኅበራዊና ባህሪ ለውጥ ጉባዔ በኢትዮጵያ የማኅበራዊና ባህሪ ለውጥ ለማምጣት የተከናወኑ ተግባራት ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ ተገለጸ።

የጤና ሚኒስትሯ ዶክተር መቅደስ ዳባ በጉባኤው መክፈቻ ፕሮግራም ላይ እንደተናገሩት፣ እስካሁን በጤና ዘርፍ የማኅበራዊና ባህሪ ለውጥ ለማምጣት የተከናወኑ ተግባራት አበረታች ለውጥ ማስመዝገብ ችለዋል።

በአሁኑ ወቅት የጤና ሚኒስቴር የተለያዩ የቴሌቪዥንና ሌሎች ሚዲያዎችን በመጠቀም ለሁሉም ፕሮግራሞቹ እየሠራበት ይገኛል ያሉት ሚኒስትሯ፤ በዚህም ማኅበራዊና ባህሪያዊ ለውጥ በማምጣት አምራች ዜጋ የመፍጠሩ እንቅስቃሴ አበረታች ውጤት ተገኝቶበታል ብለዋል።

ዶክተር መቅደስ እንዳሉት፤ በጤና አጠባበቅ ረገድ የሚኖር የማኅበራዊና ባህሪ ለውጥ በሽታን ለመከላከልና ጠንካራ የጤና ሥርዓት እንዲኖር ይጠቅማል። ኢትዮጵያ ለምትከተለውም የቅድመ መከላከል ፖሊሲ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል። እንደ ሀገርም በጤናው ዘርፍ በዘላቂ ልማት ግብ የተቀመጠውን አላማ ለማሳካት መሠረታዊ ስትራቴጂ በመሆን የሚጠቅም ይሆናል።

በመሆኑም የማኅበራዊና ባህሪ ለውጥ የማምጣቱ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ የሚቀጥል ሲሆን ለዚህም የአጋር ድርጅቶች ተሳትፎ ከፍተኛ ድርሻ ስለሚኖረው በቅንጅት የምንሠራ ይሆናል ብለዋል።

የኢትዮጵያ የጤና ትምህርትና ፕሮሞሽን ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ዶክተር እሸቱ ግርማ በበኩላቸው የማኅበራዊና ባህሪ ለውጥ ለማምጣት የተሠሩ ሥራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል ብለዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ማብራሪያ በጤና ዘርፍ የማኅበራዊና ባህሪ ለውጥ ለማምጣት እንደ ሀገር የተሠሩ ሥራዎች ውጤት እያስመዘገቡ ቢሆንም አሁንም መሠራት ያለባቸው በርካታ ሥራዎች አሉ። ግንዛቤ የመፍጠሩ ሥራ ደግሞ ከፍተኛ ጊዜ፤ ወጪና ሞያተኛ የሚፈልግ በመሆኑ ሁሉም የሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎ ይጠይቃል።

በአሁኑ ወቅት እየተካሄደ ያለው ጉባኤም የማኅበረሰቡን ጤና በማሻሻል ዜጎች የራሳቸው ጤና ባለቤት በመሆን እንዲጠብቁ ለማስቻል ግንዛቤ ለመፍጠር ሁኔታዎች የሚመቻቹበት ይሆናል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በጉባኤው ከሀገር ውስጥና ከውጭ የመጡ ከ400 በላይ የሚመለከታቸው አካላት ድጋፍ አድራጊዎችን ጨምሮ የሚሳተፉበት እንደሆነም ጠቁመዋል።

በቀጣዮቹ ቀናትም በርካታ ጥናቶችና ተሞክሮዎች የሚቀርቡ እንደሚቀርቡ በመጥቀስ፤ ይህም በመድረኩ ከሚኖረው የእውቀትና ልምድ ሽግግር ባለፈ ለፖሊሲ አውጪዎችና ተግባሪዎች እንዲሁም ለሚድያ ግብአት የሚገኝበት ነው ብለዋል።

ሦስተኛው የማኅበራዊና ባህሪ ለውጥ ጉባኤ በየሁለት አመቱ የሚካሄድ ሲሆን ዘንድሮም «የማኅበራዊና ባህሪ ለውጥ፤ ለዘላቂ ልማት» በሚል መሪ ቃል ለሦስት ተከታታይ ቀናት የሚካሄድ ይሆናል።

# በአማራና በትግራይ

## ለሚገኙ አራት ሺህ አርሶ አደሮች የምርጥ ዘር ድጋፍ ሊደረግ ነው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የኔዘርላንድ የልማት ድርጅት በግጭትና ድርቅ ለተጎዱ የአማራና የትግራይ ክልል አራት ሺህ አርሶ አደሮች የአትክልትና ፍራፍሬ ምርጥ ዘሮችን ድጋፍ ሊያደርግ መሆኑን አስታወቀ።



ድጋፉ በግጭትና ድርቅ ስተጎዱ አርሶአደሮች ይውሳል

የኔዘርላንድ የልማት ድርጅት ከቢኤኤስኤፍ ከተሰኘ ተቋም ያገኘውንና ለአርሶ አደሮች የሚከፋፈለውን የአትክልትና ፍራፍሬ ዘር በግብርና ሚኒስቴር ቅጥር ግቢ ትናንት ተረክቧል።

በወቅቱ የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ መለስ መኮንን (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ድጋፉ በግጭትና ድርቅ የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለማቋቋምና የአርሶ አደሩን ሕይወት ለመደገፍ ያለመ ነው።

የተደረገው ድጋፍ በኔዘርላንድ የልማት ድርጅት በኩል ለአርሶ አደሮቹ የሚከፋፈል መሆኑን ጠቅሰው፤ አርሶ አደሮች በአታክልትና ፍራፍሬ ሥራ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያግዝ ነው ብለዋል፡፡

በተደረገው የዘር ድጋፍ 291 ሄክታር መሬት ማልማት እንደሚቻል ዶክተር መለስ አመላክተው፤ ድርጅቱ ከዘር ድጋፍ ባለፈ አጠቃላይ የአትክልትና ፍራፍሬ አመራረት ሥልጠናዎችን እንደሚሰጥ ተናግረዋል።

የኔዘርላንድ የልማት ድርጅት የኢትዮጵያ ዳይሬክተር የሆኑት ጄሊ ግርሃም በበኩላቸው፤ ለአርሶ አደሮች የሚቀርቡት ምርጥ ዘሮችን የግብርናውን ምርት በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖራቸው ገልጸው፤ በቀጣይም የአርሶ አደሩን ሕይወት ለማሻሻል የተለያዩ ሥራዎች ይሠራሉ ብለዋል፡፡

ድርጅታቸው ትግራይና አማራ ክልል የሚገኙ በግጭትና ድርቅ የተጎዱ አርሶ አደሮችን መልሶ ለማቋቋም የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

የምርጥ ዘሮቹን አጠቃቀም ጭምር ለአርሶ አደሮች ለማሳየት የመስክ ላይ ስልጠና እንደሚሰጥ አመላክተው፤ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ከክልሎቹ ግብርና ቢሮዎች ጋር በጋራ እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

የአርሶ አደሩ ችግሮች የሚፈቱባቸውን ዕውቀትና ልምድ እንዲያጎለብቱ ለማስቻል የመስክ ማሳያ ትምህርት ቤቶችን ለማስፋፋት ጥረት ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

የተደረገው ድጋፍ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑን ጠቅሰው፤ የመጀመሪያውን ዙር ምርጥ ዘሮች ያገኙ አርሶ አደሮች ምርታማነታቸው መሻሻሉንና አርሶአደሮቹን ከምርቶቹ ከፍተኛ ዋጋ ማግኘታቸውን ገልጸዋል።

በቀጣይ ጊዜያት ከመንግሥት፣ ከግል ዘርፉ፣ ከሲቪል ማህበራትና ከማህበረሰቡ ጋር በመተባበር በአጋርነት ለመሥራት ድርጅታቸው ዝግጁ መሆኑን ዳይሬክተሯ ተናግረዋል።

በድጋፉ መሠረት 800 ኪሎ ግራም የቀይ ሽንኩርት፣ 666 ሺህ ኪሎ ግራም ቃሪያ፣ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ኪሎ ግራም የቲማቲም ምርጥ ዘሮች ለአርሶ አደሩ ድጋፍ ተደርጓል ብለዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የቀጣናውን ሕዝቦች ወንድማማችነት ወደላቀ ደረጃ ለማሻገር

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍም ሆነ በአፍሪካ ደረጃ የተካሄዱ የነፃነት ትግሎችን በማነቃቃት ለስኬማነታቸው የሞራል እና የመንፈስ ስንቅ በመሆን ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አበርክታለች፤ ትግሉ ተቋማዊ በሆነ መንገድም እንዲመራም በተለይም የአፍሪካውያንን የጸረ ቅኝ ግዛት ትግል በማቀናጀት የላቀ ስፍራ አላት።

በወቅቱ ከፍ ባለ ማንነትና አቅም፤ ዝግጁነት የመጣውን የጣሊያን ቅኝ ገዥ ኃይል በዓድዋ ላይ ድል የማድረግ የአሸናፊነት ትርክት፤ ለአፍሪካውያንም ሆነ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ለሚገኙ ጭቁን ሕዝቦች የፍትህና የነፃነት ትግል ትልቅ አቅም የፈጠረ፤ ትግሉ በይቻላል መንፈስ እንዲቃኝ የረዳ ነው።

የአፍሪካውያን የነፃነት ትግል፤ ተቋማዊ አቅም በጠየቀበት ወቅት የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን በመመስረት ሂደት ውስጥ የኢትዮጵያ አበርክቶ ከፍ ያለና ወሳኝ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት በደማቅ ቀለም የሚተርኩት ተጨባጭ እውነታ ነው። አሁን ላለው ትውልድም የኩራት ምንጭ ነው።

የአፍሪካውያንን ነፃነትም ሆነ የነፃነት ትግሉን ተጨባጭ ለማድረግ፤ በወቅቱ «የሞኖሮቪያ» እና «የካዛብላንካ» ቡድን በሚል ተከፍለው የነበሩትን የአፍሪካ ሀገሮች አዲስ አበባ ላይ በማገናኘትና ልዩነቶችን በማለዘብ ወደ አንድ የጋራ አቋም እንዲመጡ ያደረገችበት የታሪክ ምዕራፍ ለኅብረቱ መመስረት አልፋ እና ኦሜጋም እንደሆነ ይታመናል።

ከዚህም ባለፈ በወቅቱ ያልተቋጩ የነፃነት ትግሎችን በሞራል፤ በሥልጠና እና በሎጅስቲክ በማገዝ ትግሎቹ ስኬታማ እንዲሆኑ ያላሰለሰ ጥረት አድርጋለች። ይህም እንደ ሀገር ለአፍሪካዊ ወንድሞቻችን ነፃነት ያለንን የጸና አቋም እና ከበሬታ በተጨባጭ ያሳየንበት ነው፡፡

ከነፃነት ማግስት ጀምሮ በአህጉሪቱ የተፈጠሩ የሰላም እጦቶችን በድርድር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በሚደረጉ ጥረቶች ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ከመሆን ባለፈ፤ በተለያዩ የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች በመሳተፍ የሕይወት ዋጋ በመክፈል ለአፍሪካውያን ወንድሞቻችን ሰላም ያለንን አጋርነት በተግባር ገልጸናል።

የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት በተባበሩት መንግሥታትና በአፍሪካ ኅብረት ሰላም አስከባሪ ኃይል አማካኝነት በሩዋንዳ፣ ቡሩንዲ፣ ላይቤሪያ፣ ሱዳን ዳርፉር፣ ሶማሊያ፣ እንዲሁም በአቢዬ ግዛት የሰላም ማስከበር ተልዕኮውን በአግባቡ ተወጥቷል፤ እየተወጣም ይገኛል፡፡

በተለይም የሶማሊያ ሕዝብ በተለያዩ ወቅቶች በአልሻባብ የሽብር ቡድን የተደቀነባቸውን የጥፋት ስጋቶች ከፍ ያለ የሕይወት መስዋዕትነት በመክፈል መታደግ ችሏል። በሰላማዊ ወቅቶችም ለሶማሊያ ሕዝብ ያለውን ወገንተኝነት በተለያዩ የልማት ተግባራት በመሳተፍ በተጨባጭ አሳይቷል። በዚህም የሕዝቡ ምስክርነት አልተለየውም።

ከጉርብትና ባለፈ ከወንድምነት መንፈስ የሚመነጨው የሠራዊቱ ተልዕኮ፤ የሀገራቱን ሕዝቦች ግንኙነት ወደ አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ያሸጋገረ፤ ሀገራቱ በጥርጣሪ ከመተያየት ወጥተው በክፉ ቀን ወዳጅነት እና በወንድማማችነት መንፈስ እንዲተያዩ የተሻለ ዕድል መፍጠር አስችሏል።

በዚህም ኢትዮጵያውያን ወንድም በሆነው የሶማሊያ ሕዝብ ላይ የተፈጠሩ አደጋዎችን ከንፈር በመምጠጥ ሳይሆን በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን የሕይወት መስዋዕት በጠየቁ የግዳጅ ወረዳዎች በማሰለፍ፤ ለሶማሊያ ሕዝብ ሰላምና መረጋጋት ያለውን አጋርነት በተጨባጭ አሳይቷል።

ይህንን ተጨባጭ እውነታ በማጣመም፤ የሀገራቱን ሕዝቦች በደም የተሳሰረ አዲስ የግንኙነት ምዕራፍ በማደፍረስ፤ በሀገራቱ መካከል አለመተማመን እና ግጭቶችን ለመፍጠር የሚደረጉ ጥረቶች፤ ቀጣናውን በመረበሽ የቀጣናው ሕዝቦች አቅማቸውን አቀናጅተው የልማት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የማድረግ የቆየ ሴራ አካል ነው።

የቀጣናው ሀገራት ሕዝቦች ካላቸው የተፈጥሮ ጸጋ አኳያ፤ አሁን ላይ መለያቸው የሆነው ኋላቀርነትና ድህነት የሚመጥናቸው አይደለም፤ ሀገራቱ ያላቸውን የተፈጥሮ ፀጋ አቀናጅተው መንቀሳቀስ ቢችሉ፤ አካባቢው አዲስ የኢኮኖሚ አቅም ሆኖ ሊከሰት እንደሚችል ብዙም ለጥያቄ የሚቀርብ አይደለም።

መልከ ብዙ ከሆኑ ጣልቃ ገብነቶች የተነሳ ይህ እውነታ ተግባራዊ ሆኖ የቀጣናው ሀገራት ሕዝቦች ከጠባቂነት ሊወጡ፤ ከድህነትና ከኋላቀርነት ለመውጣት በብዙ መሻት ለመንቀሳቀስ ቢሞክሩም ስኬታማ መሆን አልቻሉም። ከዚህ ይልቅ ከግጭት አዙሪት ውስጥ ዋጋ እየከፈሉ መኖር ዕጣ ፈንታቸው እየሆነ መጥቷል።

ይህንን ችግር ለዘለቄታው ለመፍታት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት የጀመሩት የጋራ ተጠቃሚነትን መሠረት ያደረገ የሰላምና የልማት መንገድ ወሳኝ አቅም እንደሚሆን ይታመናል። ካለበትም የግጭት አዙሪት ለዘለቄታው በልማት ለመውጣትም ያላቸው አማራጭ ይኸው ነው ።

የአካባቢው ሀገራት ያላቸውን የተፈጥሮ ጸጋዎች አቀናጅተው ሊጓዙበት የሚችለው የልማት መንገድ፤ ዘላቂነት ላለው ሰላምና ልማት፤ ከዚያም አልፎ በአካባቢው ሕዝቦች መካከል ያለውን ወንድማማችነት ወደላቀ ደረጃ ለማሻገር ትልቅ አቅም ነው። ይህን አቅም እውን ለማድረግ የውጭ ጣልቃ ገብነቶችን የማይሸከም አካባቢያዊ ኅብረት መፍጠር ያስፈልጋል!።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## አፋጣኝ መፍትሔ የሚሻው የዕገታ ወንጀል

**ዳንኤል ዘነበ**

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ በውሳኔ ቁጥር 61/177 እ.ኤ.አ. ታኅሣሥ 20 ቀን 2006 በመወያየት አንድ ዓለም አቀፍ ድንጋጌ አጽድቋል። ድንጋጌው ‘Disappearance Convention’ በመባል የሚታወቅ ሲሆን፣ የሰው ልጅ በአስገዳጅ ሁኔታ ከመሰወር ለመጠበቅ የወጣ ነው። ከሚያዝያ 23 ቀን 2010 ጀምሮ በሥራ ላይ ውሏል፡፡

በድንጋጌው መሠረት፤ ሰውን በአስገዳጅ ሁኔታ መሰወር ማለት፤ እስራት፣ በጥበቃ ሥር መዋል፣ ጠለፋ ወይም አፈና ወይም ማናቸውም ዓይነት የነፃነት መነፈግ ተግባር ነው። ነፃነትን የመንፈግ አድራጎት ሁኔታውን ለሌሎች ሰዎች አለማሳወቅን ወይም የታፋኞችን ወይም የተሠወሩትን ሰለባዎች ዕጣ ፈንታ ከሕጋዊ ጥበቃ ውጪ በመደበቅ ሰዎችን ከሕግ ጥበቃ ውጪ እንዲሆኑ ማድረግ፣ አስገድዶ መሰወር እንደሆነ ይቆጠራል፡፡

የአንድ ሰው መሰወር የበርካታ ሰብአዊ መብቶች ጥሰት መሆኑንና የቤተሰቦችን መብቶች ጭምር የሚጥስ ነው፡፡ እንዲህ ያሉት ወንጀሎች በዓለም አቀፍ ስምምነቶች ሆነ በሀገር የውስጥ ሕጎች ላይ በሰው ልጅ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ሰብዓዊ ፍጡርን የማገት አድራጎት ለየትኛውም ዓላማ ተፈጽሞ ቢገኝ በምንም ዓይነት አመክንዮ ሊደገፍ ወይም ቅጣቱ ሊለዝብ የማይችል ደረቅ ወንጀል ነው፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 90 (1) ሥር በሰብዕና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ብሎ ከዘረዘራቸው መካከል በአስገዳጅ ሁኔታ ሰውን መሰወር ይገኝበታል፡፡ የወንጀሉ ደረጃ ከባድና ከነ ጭራሹ አንዳች መንግሥታዊ ምህረትን ወይም ይቅርታን የማያሰጥ እንደሆነም ሕገ መንግሥቱ ላይ በማያሻማ ቋንቋ ተቀምጧል፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ አካባቢዎች ሰዎችን አስገድዶ የመሰወር (Enforced Disappearance) ወንጀል እየጨመረ መጥቷል። የሰዎች በታጣቂዎች የመታገት ዜና እንግዳ መሆኑ ከቀረ ሰነባብቷል። ክስተቱም በተወሰኑ መጥፎ ዕጣ በገጠማቸው ሰዎች ላይ የሚከሰት ሳይሆን፣ በተለያዩ አካባቢዎች በተደጋጋሚ እና በብዛት የሚያጋጥም ስጋት ሆኗል።

እንደ ሀገር ዕገታ ተፈጸመ ሲባል መስማት የተለመደ ወደ መሆን ተሻግሯል፡፡ የጭነትም ሆነ የሰው መጓጓዣዎች የዕገታ ሰለባ ስለመሆናቸው በሰፊው ይሰማል፡፡ ከኢንዱስትሪዎች እስከ ቤተ እምነቶች የዕገታ ወንጀል ተቃጣባቸው መባሉ ተለምዷል፡፡

ከጥቂት ሳምንታት በፊት የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጄኔራል ደመላሽ ገብረሚካኤል ከፋና ቴሌቪዥን ጋር አድርገውት በነበረ ቆይታ፤ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች አሁንም ይህ ድርጊት ተባብሶ መቀጠሉን አረጋግጠዋል። ባለፉት ጥቂት ዓመታት በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ሰዎችን በማገት ገንዘብ መጠየቅ እየተለመደ መጥቷል።

ከዕገታ ጋር ተያይዞ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ለገንዘብ ወይም ለፖለቲካ ዓላማ ማስፈፀሚያ የሚውሉ ናቸው። የፀጥታ መዋቅሩን በገንዘብ በመደለል የራሳቸውን የፖለቲካ ዓላማ ማስፈፀሚያ የሚያደርጉ ግለሰቦች አሉ፤

ወንጀሉ በመንግሥት የፀጥታ መዋቅር ውስጥ በሚገኙ አንዳንድ ኃላፊነት የጎደላቸው ግለሰቦች ተሳትፎ የሚያደርጉበት መሆኑን ተደጋግሞ የሚነሳ ነው። ይህም ወንጀሉን ለመከላከል የሚደረገውን ሂደት ፈታኝ እንዳደረገው መገንዘብ ይቻላል። ሌላው የዕገታ ድርጊቱ በተደጋጋሚ የሚፈጸምባቸው አካባቢዎች ላይ ዘላቂ መፍትሔ ባለመሰጠቱ በአካባቢዎቹ የሚኖሩ ሰዎች የእገታ ሰለባ እስከመሆን ደርሰዋል። በሚታገቱበትም ወቅት ባገታቸው አካል የመብት ጥሰት፣ ጭካኔ የተሞላበት አዋራጅ አያያዝ ወይም ቅጣት ይደርስባቸዋል። እንዲሁም ቁጥራቸው አነስተኛ የማይባሉ ሰዎች ሕይወታቸው እስከማለፍ ደርሷል።

በዚህም ዜጎች ደህንነት እንዳይሰማቸው፤ በነፃነት ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የዕለት ተዕለት ተግባራቸውን ለማከናወን እንዲቸገሩ እና ኑሯቸው ስጋት የተሞላ እንዲሆን አድርጎታል። በተጨማሪም ድርጊቱን የሚፈጽሙት ሽፍቶች ከመከላከያ ወይም ከፖሊስ ጋር ፊት ለፊት የሚታኮሱ አይደሉም። ተደብቀው ሕዝብ ላይ ችግር የፈጥሩ ስለሆኑ ሁኔታውን አስቸጋሪ አድርጎታል።

ይሁንና ፌዴራል ፖሊስ ሆነ መከላከያ የኅብረተሰብ ደህንነትን ከማስጠበቅ አንፃር ኃላፊነቱን ለመወጣት ያላሰለሰ ጥረት እያደረገ እንደሆነ የሚካድ አይደለም። በዚህም የጸጥታ አካላት ወንጀሎቹን ለመከላከል በቅንጅት ውጤታማ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ በተጨባጭ አሳይተዋል።

ለምሳሌ የካቲት 11 ቀን 2016 ዓ.ም ክስተት እናንሳ፡ የሀገር መከላከያ ሠራዊት በማኅበራዊ ገጹ አንድ መረጃ ይፋ አድርጓል። ማንሻውን ከአዲስ አበባ በማድረግ ወደ ደዴ ከተማ በመጓዝ ላይ የነበረ ሀገር አቋራጭ አውቶቡስ በሆሮ ጉድሩ ሀቦቦ ከተማ በአሸባሪው የሸኔ ቡድን ታግቶ ነበር። የሀገር መከላከያ ሠራዊት ባደረገው ተጋድሎ ተሸከርካሪውን ጨምሮ ሰዎችን ማስለቀቅ ችሏል።

ይህን ጠቀስን እንጂ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በድርጊቱ የተሳተፉ ግለሰቦችን እና ቡድኖችን ተከታትሎ በመያዝ ተጠያቂ ሲሆኑ አይተናል፡፡ ይህም ሆኖ ግን ወንጀሉ እየተስፋፋ ካለበት ደረጃ አንጻር ገናብዙ መሥራት እንደሚጠበቅ መገመት የሚከብድ አይደለም። ወንጀሉን የመከላከል እና መቆጣጠር ተግባር የሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ፣ ቁርጠኝነት እና የጋራ ርብርብ ይጠይቃል።

**ወንጀሉን የመከላከል እና መቆጣጠር ተግባር የሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ተሳትፎ፣ ቁርጠኝነት እና የጋራ ርብርብ ይጠይቃል**

በሕገ መንግሥቱ ላይ እንደተቀመጠው የወንጀሉ ደረጃ ከባድና ከነ ጭራሹ አንዳች መንግሥታዊ ምህረትን ወይም ይቅርታን የሚያሰጥ አይደለም። በዚህ የወንጀል ድርጊቱ ተሳትፎ የሚያደርግን ማንኛውንም አካል መንግሥት ለሕግ ማቅረብ ግዴታ አለበት። የጸጥታ መዋቅሩንም በመፈተሽ ውስጡን ማጥራት ይጠበቅበታል። ለዚህ ጊዜ ሊሰጥ አይገባም።

የፌዴራል መንግሥት ሆነ የክልል የጸጥታ አካላት በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚፈጸሙ እገታዎችን ለመከላከል የጀመሩትን ጥረት አጠናክረው ሊቀጥሉ፤ ኅብረተሰቡም መንግሥት ወንጀሉን ለመከላከል እና በድርጊቱ የተሳተፉ ግለሰቦችን በቁጥጥር ስር ለማዋል የሚያደርገውን ጥረት ሊደግፍ ይገባል። ወንጀሉ በሚፈጸምበት ጊዜ ድርጊቱ የተፈፀመባቸው ግለሰቦች መረጃውን በሰዓቱ ለፖሊስ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል። ይህ ደግሞ ወንጀለኞችን ተከታትሎ የመያዝ ጥረቱን አስቸጋሪ እንዳይሆን ያደርገዋል።

በአጠቃላይ ድርጊቱ « እቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም » እንደሚባለው በተለያዩ አካባቢዎች ብቅ ብቅ እያለ የሚገኘውን የዕገታ ድርጊት መንግሥት በፍጥነት መቆጣጠር ካልቻለ፤ የወንጀሉ መስፋት በማኅበረሰቡ ላይ እያደረሰ ካለው ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጫና አልፎ በሀገር ገጽታ ላይ ከፍተኛ የሆኑ ተጽእኖ መፍጠሩ የማይቀር ነው።

# ‹‹በዞናችን የማዕድን ጉዳይ መስመር የያዘው አሁን ነው››

አቶ ነጋሽ ቡላላ የጉጂ ዞን ዋና አስተዳዳሪ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**የጉጂ ዞን በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ ሰፋፊ ዞኖች አንዱ ነው፤ በተፈጥሮ ሃብትም የታደለ፤ በተለይም ደግሞ በሀገሪቱ ትልቅ የወርቅ ክምችት አለበት ከሚባሉ ስፍራዎች አንዱ ነው። ቡና የሚበቅልበት የአረንጓዴ ወርቅ መናኸሪያም፤ በእንስሳት ሃብት፣ በማር እና በደን ልማትም ስመ ገናና ከሆኑ አካባቢዎች መካካል ነው። ከዚህም ባሻገር የገዳ ሥርዓት በፅኑ ስር የሠደደበትና አሁንም ድረስ ሳይሸራረፍ፣ ባህል፣ እሴትና ወጉ ጭምር ሳይበረዝ የሚተገበርበት አካባቢ ነው።**

**በሌላ ጎኑ ሰፊ ኢንቨስትመንት የሚካሄድበትን ያክል ዕድገት ያልተመዘገበበት ዞን ነው። በተለይም በማዕድን ልማት ዙሪያ በነዋሪዎች ለዓመታት ቅሬታዎች የሚቀርቡበት አካባቢ ነወ። በዛሬ ዕትማችን በእነዚህና ሌሎች ጉዳዮችን አንስተን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል እና የጉጂ ዞን ዋና አስተዳዳሪ ከሆኑት አቶ ነጋሽ ቡላላ ጋር ቆይታ አድርገናል፤ መልካም ንባብ።**

**አዲስ ዘመን፡- ጉጂ ዞን እና አሁናዊ ገፅታዋ እንዴት ምን ይመስላል ?**

**አቶ ነጋሽ፡-** ጉጂ ዞን በሰፊው የሚገለፅ ነገር አላት። የሕዝቡ አኗኗር አጠቃላይ ሲታይ ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል አኳያ የተፈጥሮ ሃብትና ሕዝብ በሚገባ ተጣምሮና ተዋዶ የሚኖርባት ዞን ናት። በጉጂ ዞን ሁሉም የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች አሉባት ማለት አንችላለን። ዞኑ በጠንካራ የገዳ ሥርዓትም የሚታወቅ ነው። በእርገጥ የገዳ ሥርዓት በሌላ ቦታም አለ። ነገር ግን ጉጂ ውስጥ ከጥንት ጀምሮ ሥርዓቱ ሳይቋረጥ የቀጠለበት እና ያበበበት ነው።

ይህ ሥርዓት ከዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ስለመኖሩም አንዳንድ ጥናቶች ያሳያሉ። ይህም በዞኑ የገዳ ስርዓትን ለረጅም ዘመናት ሲተገበር እንደኖረ ማሳያ ነው። በዚህም ጎን ለጎን ዞኑ በደን ልማት እና በለምነቱ ይታወቃል።

**አዲስ ዘመን፡- በጉጂ ያለው የደን ልማት ምን የተለየ ገጽታ አለው?**

**አቶ ነጋሽ፡-** እዚህ አካባቢ ደን ማለት ሕይወት ነው። ደን ልማት ከገዳ ሥርዓት ጋር ይያያዛል። በጉጂ ውስጥ ደን ማለት ልክ የሰው ሕይወት ያክል ቦታ የሚጠው ነው። ደን ማንም ብድግ ብሎ አይጨፈጭፍም። የመኖር ሚስጥር እና ሕይወት ነው ተብሎ ይታሰባል። በዚህም የተነሳ ለዘመናት ሳይነካ የኖረ እና በመቶ ሺህ ሄክታር የሚቆጠር ደን አለ። በደን ሽፋን ከኦሮሚያ ዞኖች ቀዳሚው ነው። በጣም ጥቅጥቅ ያለ ደን ያለበት ነው። ሕዝብ እየተበራከተ ሲሄድ ደን ይጨፈጨፋል ብለን ስለንምንሰጋም የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ቀይሰንም እየሰራን ነው። ይህ ለደን ልማት ካለን ፍላጎት እና ልዩ ትኩረት የመጣ ነው።

በገዳ ሥርዓትም ደን ማለት ሕይወት በመሆኑ ደን ሲጨፈጭፍ የተያዘ አካልም ከፍተኛ ቅጣት ይጠብቀዋል። ይህ በመሆኑም ነው ጉጂ ያለው ደን እና የሰው ልጅ ትስስር ጠንካራ ነው የምንለው። በዞናችን በግብርና እና በአጠቃላይ የሕዝብ የሰፈረበት ቦታ ሲደመርና በደን ከተሸፈነው ጋር ሲነፃፀር በደን የተሸፈነው ይበልጣል። ደን መጠበቅ አለብን ከሚል እሳቤ ደግሞ አዲስ ስትራቴጂ ዘይደናል።

**አዲስ ዘመን፡- ምን የተለየ ስትራቴጂ አላችሁ?**

**አቶ ነጋሽ፡-** በዞኑ ከፍተኛ የደን ሽፋን መኖሩ የሚታወቅ ነው። ይህ መጠበቅ አለበት። ነገር ግን ደግሞ ከዚህ በተለየ ሁኔታ አንዳንድ አዳዲስ ሐሳቦችን ማፍለቅ አለብን ብለን አስበናል። ከምዕራብ ጉጂ እስከ ባሌ ድረስ ጥቅጥቅ ያለ ደን ሽፋን ያለበት ነው። እኛም በጉጂ ዞን ውስጥ 29ሺ ሄክታር ደን ጥብቅ ደን እና ብሔራዊ ፓርክ እንዲሆን እየከለልን ነው። ይህን የምንከልለው ደግሞ ብዙ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ ነው።

የመጀመሪያው የአካባቢ የአየር ንብረት ከቀድሞ በተለየ ሁኔታ እንዳይቀየር ነው። ይህ እንደ ሀገርም ፋይዳው የጎላ ነው። ሌላው እንደ ሀገር ግሪን ኢኮኖሚ አኳያ ዘርፈ ብዙ ትርጉም ያለው በመሆኑ ነው። ደን እንዳይሳሳ እና እንዳይጨፈጨፍም ጥበቃ ያገኛል። በአጠቃላይ በሀገሪቱ የተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ መሰረቱ እንዲጠናከርና ኢትዮጵያም በዚህ ረገድ በዓለም ዘንድ ያገኘችው ከፍተኛ ትኩረት የበለጠ ትርጉም እንዲኖረው በማሰብ ጭምር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ዞኑ ከደን ልማት በዘለለ የሚታወቀው በማዕድን ጭምር ነው። በዚህ ላይ የሚጠበቅባችሁን እየሰራችሁ ነው?**

**አቶ ነጋሽ፡-** ዞኑ ለኢንቨስትመንት በጣም ምቹ ከሚባሉት ውስጥ አንዱ ነው። በ2016 በጀት ዓመት 143 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ወደ ሥራ ገብተዋል። በቀጣይ ይህን ለማሳደግና 700 የሚሆኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ለማስገባት እየሰራን ነው። እንደ ኦሮሚያ ክልል ደግሞ ከፍተኛ የማዕድን ክምችት ያለበት ዞን ጉጂ ዞን ነው። እስከ አሁን በጥናት የተለዩ 53 የሚደርሱ ማዕድናት እንዳሉም ይታወቃል።

ከእነዚህ ውስጥ 31 የሚሆኑት ተለይተው አንዳንዶቹ እየተመረቱ ነው፤ ለአንዳንዶቹ ደግሞ ገበያ ፍለጋ ላይ ነን። ይህ የሚሳያው አካባቢው በከፍተኛ ደረጃ በማዕድን የበለፀገ ስለመሆኑ ነው። በሌላ አካባቢ የሌሉ እና በጉጂ ብቻ የሚገኙ እጅግ በዋጋ ደረጃ በጣም ውድ፣ በዓለም ገበያ ደግሞ በእጅጉ ተፈላጊ የሆኑ ማዕድናትም ይገኛሉ።

**አዲስ ዘመን፡- የማዕድን ሃብት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ነዋሪው ሕዝብ ከዚህ ሃብት እየተጠቀመ ነው?**

**አቶ ነጋሽ፡-** ተጠቃሚነትን በተመለከተ የአካባቢው ሕዝብ በተለይም ወጣቶችን አደራጅተን እንደየአስፈላጊነቱ እየተጠቀሙ ነው። በተለይ በወጣቶች አደረጃጀት በተመለከተ የሥራ ዕድል ፈጠራ ሴክተር አደራጅተን በትኩረት እየሰራን ነው። በመሆኑም 121ሺ የሥራ ዕድል ለመፍጠር አቅደን እስካሁን በማዕድን ዘርፍ ላይ ብቻ 50ሺ ዜጎች ተጠቃሚ ሆነዋል። በዚህ ሴክተር የተፈጠረው የሥራ ዕድል በጣም ብዙ ነው። በዚህ ውስጥ የሚንቀሳቀሰው የገንዘብ መጠንም በጣም ከፍተኛ ነው።

**አዲስ ዘመን፡-ወጣቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ሲባል ብቻ ወጣቶችን አደራጅቶ ማሠማራት ተገቢ ቢሆንም፤ የማዕድን ዘርፉ ልዩ እውቀት፣ ቴክኖሎጂ እና ጥበብ አይፈልግም?**

**አቶ ነጋሽ፡-** ማዕድናት ክፍፍል ወይንም ዘርፍ አላቸው። የከበሩ ማዕድናት የሚባሉ አሉ። በሌላ ጎኑ ደግሞ በዞኑ ውስጥ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚያገለግሉ ማዕድናት ብለን ከፍለን በየዘርፉ እየሰራን ነው። አንዳንዶቹ ማዕድናት በፌደራልና በክልል መንግስት ብቻ ስምሪትና ፈቃድ ሊሰጡ ይችላሉ። የሀገር ብሔራዊ ጥቅምና ደህንነት ቅድሚያ ይሰጠዋል። አንዳንዶቹ ደግሞ መደበኛው ማኅበረሰብ ሊጠቀመው የሚችለው ነው።

እኛም እነዚህን ሁኔታዎች ታሳቢ አድርገን ነው የምንሰራው። ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚውሉ ማዕድናት ላይ ወጣቶችን አደራጅተን እየተጠቀሙ ነው። ለአብነትም ለኮንስትራክሽን እና ለተለያዩ ግንባታዎች ግብዓት የሚሆኑና ውስብስብ ዕውቀት የማይጠይቁ ማዕድናት አሉ። በአጠቃላይ ሲታይ ግን ማዕድናት ላይ ከፍተኛ አቅም ያለው የሰው ኃይል ማሰማራት እንደሚቻል ተገንዝበን ወደ ሥራ ገብተናል።

በአርብቶ አደርም ሆነ አርሶ አደር አካባቢ ይህን ተግባራዊ አድርገን ወጣቶች ተጠቃሚ ሆነዋል። እያንዳንዱን ሥራ በኃላፊነት የምንሰራው መሆኑን በሚገባ ማጤን ይገባል። በብዛት እየሰራን ያለነው ወጣቱ ከዝቅትኛ አቅም ተነስቶ ወደ ከፍተኛ ደረጃ መሸጋገር አለበት በሚል እሳቤ ነው።



ፎቶ - ገበዩ ገብሬ

**በወጣቶች አደረጃጀት በተመለከተ የሥራ ዕድል ፈጠራ ሴክተር አደራጅተን በትኩረት እየሰራን ነው። በመሆኑም 121ሺ የሥራ ዕድል ለመፍጠር አቅደን እስካሁን በማዕድን ዘርፍ ላይ ብቻ 50ሺ ዜጎች ተጠቃሚ ሆነዋል**

**አዲስ ዘመን፡- ወጣቱ በመደራጀቱ ብቻ ወደ ሌላ ደረጃ መሸጋገር ይችላል ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ነጋሽ፡-** እኛ ወጣቶችን አደራጅተን የሥራ ዕድል እንዲያገኙ የምናደርገው በዚያው እንዲቆዩ አይደለም። ከጥቃቅን ተነስተው፣ ወደ መካከለኛ ኢንዱስትሪ እንዲያድጉ አስበን ነው። ከሥር ከሥሩ ደግሞ ሌላ ይተካል። ከመካከለኛው ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ አድገው ሀገርን እንዲጠቅሙ ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ በርካታ አስቻይ ሁኔታዎች አሉ። ለምሳሌ ለምርጥ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከኦሮሚያ ማዕድን ባለስልጣን ጋር በመነጋገር ማሽኖችን የሚያገኙበት ዕድል እየተፈጠረ ነው።

ወርቅ ላይ ጥሩ እየሰራን ነው። በሌሎች ማዕድናትም ላይ እየሰራን ነው። በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ ወጣቶቹ ተደራጅተው ጥሩ ሥራ እየሰሩ እያለ የገበያ ችግር ያጋጥማቸዋል። ዞናችን ከማደራጀት ጀምሮ አቅሙ የሚችለውን ሁሉ ያግዛል። ችግሮችን ለማቃለል ከኦሮሚያ ማዕድን ባለስልጣን እና ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር መፍትሄ እያበጀን ነው። በትልልቅ ድርጅቶችም ደረጃ ራሳቸውን በየጊዜው እንዲያሳድጉ ነው ድጋፍ እናደርጋለን። በአጠቃላይ ግን ማኅበረሰቡ ተጠቃሚነት እንዲሆንና የአካባቢ ሃብትም በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል እየሰራን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በዞኑ ውስጥ ከፍተኛ አቅም ያላቸው ድርጅቶች ኢንቨስትመንት እያካሄዱ ነው። ይህም ሆኖ ማዕድናት ባሉበት አካባቢ ኮንትሮባንድ ስጋት መሆኑ ይታወቃል። ስጋቱን ስለመቀልበስ ምን እየሰራችሁ ነው ?**

**አቶ ነጋሽ፡-** ትክክል ነው። ማዕድን በባህሪው በጣም ሕገ ወጥ ንግድ እና ለፈጣን የኮንትሮባንድ

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ተጠየቅ

# ‹‹በዞናችን የማዕድን ጉዳይ...

**ከገጽ 6 የዞረ**

ዝውውር የመጋለጥ ዕድል አለው። ባለው ተጨባጭ ሁኔታ እና ተፈላጊነት አኳያም በጣም ተጋላጭ የሆነ ዘርፍ መሆኑም የሚታመን ነው። እኛም ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት ‹‹ታክስ ፎርስ›› አዘጋጅተን እየሰራን ነው። ለአብነትም እኛ ከኦሮሚያ ማዕድን ባለስልጣን እና ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር የተናበበ ሥራ እየሰራን ነው። ነገር ግን ሙሉ ለሙሉ ችግሩን ፈትተናል ወይንም ደግሞ የመጨረሻውን እልባት ሰጥተናል ማለት አንችልም።

ቀደም ሲል በርካታ ችግሮች ነበሩ። ማዕድን የሀገሪቱን የምጣኔ ሃብት ዕድገት ወይንም የኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነትን ይወስናሉ ወይም በኢኮኖሚው ውስጥ ወሳኝ ናቸው ተብለው ከተመደቡ ዘርፎች መካካል እንደ አንዱ የተቆጠረው ከለውጥ ወዲህ ነው። ቀደም ሲል የተሰጠው ትኩረት አናሳ በመሆኑም ለችግር የመጋለጥ ዕድል ነበረው።

ቀደም ሲል ሀብቱ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ውጭ ይወጣ ነበር፤ ጥቂቶችም ይጠቀመበት ነበር። እንደ አጠቃላይ ሲታይ ሀገርንም የሚጎዳ ሥራ ይከናወን ነበር። አሁንም ቢሆን ሙሉ ለሙሉ የማዕድን ኮንትሮባንድን ንግድ አስቀርተናል ባይባልም ቀደም ሲል ከነበረው ሕገ ወጥ አሰራርን ከማስቀረት አኳያ ግን ከፍተኛ መሻሻል ይታያል። ሀገርና ሕዝብን በመጉዳት የጥቂት ግለሰቦችን ኪስ የማጨቅ ባህሪ እና ዝንባሌ አሁን የለም።

**አዲስ ዘመን፡- በጉጂ ውስጥ ማዕድን ልማት ላይ ከፍተኛ ቅሬታ የሚቀርብበት እንደነበር ይታወቃል። በተለይም ለገደንቢ የወርቅ ማምረቻ እንደ አብነት ማንሳት ይቻላል። አሁንስ ቅሬታዎች የሉም?**

**አቶ ነጋሽ፡-** ከለውጡ በፊት የነበሩ ቅሬታዎች ትክክለኛ ነበሩ። እነዚህ ቅሬታዎች ቀደም ሲል የነበሩ ናቸው። ከለውጡ በኋላ ግን መፍትሄ አግኝቷል። መንግስትም ሕዝብ ተጠቃሚ እንዲሆን አቅጣጫ አስቀምጦ ወደ ተግባር ተገብቷል። ድርጅቶችም የነበራቸውን ብልሹ አሰራሮች እንዲያርሙ ተደርጓል። ማኅበረሰቡ ከአካባቢው ከሚገኘው ሃብት እንዴት ተጠቃሚ ይሆናል በሚለው ላይ አሰራር አለ። የሕዝቡ ተጠቃሚነት ምን መሆን አለበት የሚለው በሚለው ሕግ ወጥቷል። ይህንንም ከቀበሌ ጀምሮ በወረዳ፣ ዞን፣ ክልል እና ፌደራል ደረጃ ማን ምን ይሰራል የሚለው አሰራር ተቀምጧል።

ቀደም ሲል ከሕዝብ ጋር ያለው ግንኙትም ጥሩ አልነበረም፤ አሁን ይህ ተስተካክሏል። በእርግጥ ኢንዱስትሪ ሲቋቋም ከችግር ነፃ ነው ማለት አይቻልም። ይሁንና ይህን መፍታት የእኛ ድርሻ ነው። እኛም ወጣቶችን ስናደራጅ ወደ ተሻለ ቦታ እንዲደርሱ እና ኅብረተሰቡም እንዲጠቀም ነው። ሕብረተሰቡም ቀደም ሲል የነበረው ቅሬታ መፈታቱን ያምናል። ቀደም ሲል የነበረውና ለዓመታት የነበረው ችግር አሁን የለም። እኛም ለበለጠ ዝግጁነትና ጥንቃቄ ጥናቶችን እያካሄድን ነው። በአጠቃላይ ሲታይ ግን፤ በዞናችን የማዕድን ጉዳይ መስመር የያዘው አሁን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን እንዳይደገሙ ቀደም ሲል የነበሩት ችግሮች ምንጫቸው ተለይቷል?**

**አቶ ነጋሽ፡-** የማዕድን ዘርፍ ትልቁ ችግር እና ድሮም የተበላሸው ከአሰራር ነበር። ቀደም ሲል በነበረው አሰራር ግልፅነት የጎደላቸው በርካታ ጉዳዮች ነበሩ። አንዳንድ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ማዕድን ሰብስበው ጭነው ወደሚፈልጉበት ቦታ ይወስዱ ነበር። ጠያቂ የሌለው በመሆኑ ሃብት ይባክን ነበር። ዋነኛ የቅሬታ ምንጭ ከሆኑትም ውስጥ አንዱ ይህ ነው። በአሁኑ ወቅት ከቀበሌ ጀምሮ በእያንዳንዱ የመንግስት የስልጣን እርከን ላይ ያለ ሕጋዊ አካል ኃላፊነቱ ምንድን ነው፤ ምንስ ይሥራ የሚለው ተለይቷል።

አሁን ከሮያሊቲ ክፍያ ጀምሮ ማዕድንን በተመለከተ ከማን ምን ይጠበቃል የሚለው ሕጋዊ አሰራር ተቀምጦለታል። በዚህም የተነሳ ሕዝብን ችግር ውስጥ የሚከት ነገር የለም። በፊት የነበረውን አሁን እንዳለ አድርጎ መውሰድ አግባብ አይደለም። እኛ ከሕዝቡ ጋር በቅርበት እየተወያየንና መፍትሄ እየሰጠ ነው። ችግሮች ቢፈጠሩ እንኳን በፍጥነት ለመመለስ የሚያስችል ሕጋዊ አሰራር ዘርግተናል። ይህ ከፌደራል ጀምሮ እስከ ታች ድረስ የወረደ በመሆኑ አሁን ስጋት

**የማዕድን ዘርፍ ትልቁ ችግር እና ድሮም የተበላሸው ከአሰራር ነበር። ቀደም ሲል በነበረው አሰራር ግልፅነት የጎደላቸው በርካታ ጉዳዮች ነበሩ። አንዳንድ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ማዕድን ሰብስበው ጭነው ወደሚፈልጉበት ቦታ ይወስዱ ነበር**



የለም።

**አዲስ ዘመን፡- እንደ ሀገር ኮንትሮባንድ ንግድ ካስባቸው አካባቢዎች አንዱ ጉጂ ዞን ነው። ይህን በመከላከል ላይ ምን የተሰራ ነገር አለ?**

**አቶ ነጋሽ፡-** በኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን ከለውጡ በፊት እጅግ አስቸጋሪ የሆነ የኮንትሮባድ ንግድ ነበር። ሕገ ወጥነት ያለበት ዘርፍ አንዱ ማዕድን ነው። ሌላው በዚህ አካባቢ ኮንትሮባንድ የሚነሳው በኬኒያ ሞያሌ በኩል የሚገቡ የተለያዩ የኮንትሮባንድ ሸቀጦች አሉ። ይህንን ለመከላከል ከፍተኛ ቁጥጥር እያደረግን ነው። ጠንካራ ሥራዎችን በመስራታችን ውጤት ተገኝቷል። ባለፉት አምስት ወራት ብቻ 40 ሚሊዮን ብር የሚገመት የኮንትሮባንድ ሸቀጦች በቁጥጥር ሥር አውለናል። ቀደም ባሉት ዓመታት ከኮንትሮባንድ ንግድ ከሁለት ሚሊዮን ብር የዘለለ አንሰበስብም ነበር።

ሕገ ወጥ ንግድ እና ኮንትሮባንድን በመከላከልና በመቆጣጠር ረገድ ሰፊ ሥራ ሰርተናል። በአሁኑ ወቅትም ቢሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በተቀናጀ ሁኔታ እርምጃ እየወሰድን ነው። በተለይም ማዕድናት፣ አልባሳትና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች በብዛት በኮንትሮባንድ ዝውውር ውስጥ መኖራቸውን ተገንዝበናል።

አሁን የኮንትሮባንድ ንግድ ጉዳይ አሳሳቢ አይደለም። ይህን ለማስቀረት ብዙ ሰርተናል። የመጀመሪያው ማዕድን ትክክለኛ ገበያ ላይ እንዲቀርብ እና ተገቢውን ዋጋ እንዲያገኝ ማድረግ ነው። ሌላኛው ደግሞ ከማኅበረሰቡ ጋር ያለንን ጠንካራ ቁርኝት ማሳደግና ችግሮችን በውይይት መፍታት ብሎም ግንዛቤ ማሳደግ ነው። በዚህም ስኬታማ የሚባሉ ክንውኖች አሉ።

ኅብረተሰቡም አሁን ላይ ከኮንትሮባንድ ንግድ ይልቅ ሕጋዊ መሆኑን አዋጭ መሆኑን እየተገነዘበ ነው። የቁጥጥር ሥርዓታችንም ከተለመደው አካሄድ በተለየ መንገድ ስትራቴጂን እና ዕውቀትን መሰረት ያደረገ ነው። በዚህ የተነሳ አበረታች ውጤቶችን አስመዝግበናል። በቀጣይም አጠናክረን የምንቀጥለው ነገር ቢኖር ኮንትሮባንድ ንግድን ለማስቆም የምናደርገው ጥረት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ጉጂ ዞን ከሠላም እና መረጋጋት አኳያ አልፎ አልፎ ጥያቄዎች ይነሱበታል። አሁንስ?**

**አቶ ነጋሽ፡-** ሰዎች በርቀት ሆነው ጉጂ ሠላም የሌለ ይመስላቸዋል። እኔ ግን አንድ ነገር ማሳወቅ የምፈልገው ጉጂ በጣም ሠላም ነው። በዞናችን ውስጥ 13 ወረዳዎች አሉን። 11 ወረዳዎች ሙሉ ለሙሉ ፀጥታ ችግር የለባውቸም። ሁለቱ ወረዳዎችም ከሁለት ቀበሌ የማይበልጡ ብቻ አልፎ አልፎ የተወሰነ ችግር አለ። እነዚህም ከምስራቅ ቦረና ጋር የሚዋሰኑ ወረዳዎች ናቸው።

ይህም ሆኖ በአሁኑ ወቅት ስልታዊና ውጤታማ ኦፕሬሽኖችን እያካሄድን ጠላት የሚንቀሳቀስበት ቀጣና አሳጥተናል። ስለዚህ ጉጂ ሰላም ነው። የሠላሙ ምንጭ ደግሞ ኅብረተሰቡ ነው። ሕዝቡ ይህን የተማረው ከገዳ ሥርዓት ነው። በገዳ ሥርዓት ውስጥ ሠላም ቅድሚያ ይሰጠዋል። በመሆኑም የአባገዳዎች እና የሕዝቡ ሚና ቀላል አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ የፀጥታ መዋቅራችን ትልቁን ኃላፊነት እየተወጣ ነው። ሚሊሻዎች፣ የኦሮሚያ ክልል ፖሊስ፣ የፌደራል ፖሊስ እና የሀገር መከላከያ ሰራዊት ለሠላምና መረጋጋቱ ትልቅ አበርክቶ አላቸው። በመሆኑም ሁሉም ወረዳዎች በልማት ላይ ናቸው። ልማት ማካሄድ የሚፈልግ ማንኛውም አካል ወደ ዞኑ መጥቶ ኢንቨስት ማድረግ እንደሚችል በዚህ አጋጣሚ መልዕክት ማስተላለፍ እወዳለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ሳደረጉት ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ነጋሽ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ።

# ሀገራዊ የሸማቾች መብት ጥበቃ ማኅበር ቦርድ ተመሠረተ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

**አዳማ፡-** ሁሉንም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ያቀፈ ሀገራዊ ውክልና ያለው በሀገሪቱ የመጀመሪያው የሸማቾች መብት ጥበቃ ማኅበር ቦርድ ተመሠረተ።

በሸማቾች መብት ጥበቃና በማኅበራት አስፈላጊነት ዙሪያ ከክልል ለመጡ የሸማቾች ማኅበር አመራሮች የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ትናንት በአዳማ ከተማ ሰጥቷል።

በሥልጠናው ወቅት የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የንግድ ሥርዓትና ላይሰንሲንግ ዘርፍ የሚኒስትር ዴኤታ አማካሪ አቶ ግዛው ተክሌ እንደተናገሩት፤ ሸማቹ ማኅበረሰብ በጋራ መብቱን የሚጠይቅበትና የሚያስከብርበት ሁሉንም ክልሎችና ሁለቱን ከተማ አስተዳደሮች ያቀፈ ሀገራዊ ውክልና ያለው በሀገሪቱ የመጀመሪያው የሆነ ሀገራዊ የሸማቾች መብት ጥበቃ ማኅበር ቦርድ ተመስርቷል።

የሸማቾች ማኅበራት መደራጀታቸው ከሚሰጠው ጠቀሜታ አንዱና ዋነኛው ሸማቹ ማኅበረሰብ መብቱን ተገንዝቦ ለመብቱ እንዲታገል ማስቻል ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ግዛው ማብራሪያ፤ ሌላው የሸማቹን አማርጦ የመግዛት ባህልን በማዳበር ፍትሃዊ የንግድ ሥርዓት እንዲሰፍን ያስችላል። በተጨማሪም አንድ ሰው ያለፍላጎቱ እንዲገዛ የሚደርስበትን ጫና ለማስወገድ እንዲሁም በጋራ መብቱን ለመጠየቅ ያግዛል።

ማኅበሩ እንደሀገር በቦርድ እንዲመራ መደረጉ ሸማቹ ማኅበረሰብ ቅሬታውን የት ማቅረብ እንዳለበት እንዲረዳና ጥያቄው ምላሽ እንዲያገኝ ከማስቻል አንፃርም ፋይዳው የጎላ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ ግዛው፤ እንደሀገር የሸማቾች መብት ጥበቃ ማኅበር ቦርድ መመስረቱ ደግሞ የሸማቹን መብት ከማስጠበቁ ባለፈ ሀገርን ወክሎ የተለያዩ የንግድ ተግባራትን ለማከናወን እንደሚያግዝ ገልጸዋል።

ሸማቹ ማኅበረሰብ መብቱን ተረድቶ በአግባቡ መጠቀም ላይ ውስንነት እንዳለበት አመላክተው፤ የቦርዱ መመስረት «የኔ ነው» በሚለው አካል ማኅበረሰቡ ስለመብቱ ተገንዝቦና መብቱን አውቆ እንዲተገብር ስለሚያስችል የተሻለ ውጤት ለማምጣት እንደሚያግዝ ተናግረዋል።

በሚኒስቴሩ የሸማቾች መብት ጥበቃ ግንዛቤ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሰይፉ አየለ በበኩላቸው፤ እንደ ሀገር ገበያው እየሰፋ መምጣቱን ተከትሎ በዚያው ልክ የሸማቾች መብት ጥሰት እየተበራከተ ነው ብለዋል።

ችግሩን በመንግሥት መዋቅር ብቻ መፍታት ስለማይቻል ሀገር አቀፍ የሸማቾች መብት ጥበቃ ማኅበር ቦርድ በክልልና ከተማ አስተዳደሮች መመሥረቱ የሸማቹን መብት የሚያስጠብቁ ልዩ ልዩ ዘመቻዎችን ለማድረግ፣ የሕዝብ ድምጽ ለመሆን፣ ለሸማቹ ግንዛቤ ለመፍጠር፣ የገበያ መረጃን በቀላሉ ለመለዋወጥ እንደሚያግዝ አብራርተዋል።

እንደሀገር መብትን ያለማወቅና ያለመገንዘብ ችግር ብቻ ሳይሆን እያወቁም ማጥፋት ጭምር እንደሚስተዋል አመላክተው፤ የማኅበራት ቦርድ መኖሩ የአባላቶቻቸውን መብት ከማስከበር በተጨማሪ ማኅበራዊ ኃላፊነትን ለመወጣት፣ ሕገወጥ ነጋዴዎችን ከገበያው ለማስወጣት፣ በነጋዴና ሸማቹ መካከል መልካም ትስስርን ለመፍጠር፣ በዘርፉ አላሠራ ያሉና አሳሪ ሕጎች እንዲሻሻሉ ለማድረግ ያግዛል ሲሉ አስረድተዋል።

የቦርዱ መመስረት የሸማቹን ማኅበረሰብ ጥቅም በሚያስጠብቅ መንገድ የመንግሥትን ፖሊሲና ስትራቴጂ ጭምር ማስቀየር የሚያስችል ሥራ ለመሥራት ያግዛል። ሀገርን ከገቢ አንፃር ብቻ ሳይሆን ከተለያዩ ሉላዊ ተጽዕኖና ጉዳት የሚታደግ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የሸማቾች መብት ጥበቃ ማኅበር ቦርዱ በመጪው መጋቢት ወር፣ የዓለም የሸማቾች ቀን ክብረ በዓል ላይ እውቅና እንደሚሰጠው ተጠቁሟል።

# 20 ሚሊዮን ወጣቶችን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሚኒስትሯ፤ ወጣቶች በሀገሪቱ ለውጥ ለማምጣት ወጣቶች የልቦና ውቅራቸው ተስተካክሎ በመልካም ስብዕና ታንጸው ለሀገርና ለትውልድ እንዲተርፉ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ወጣቶች ከሱስ ተላቀው አምራችና ብቁ ዜጋ መሆን እንዲችሉ የልቦና ውቅራቸው በተገቢው መንገድ መገንባት እንዳለበት በመግለጽ፤ የአስተሳሰብ ለውጥና የልቦና ውቅር ግንባታ ላይ ካልተሠራ የመልካም ስብዕና ተጻራሪ ለሆኑ ነገሮች ተጋላጭ እንደሚሆኑ ጠቁመዋል።

የልቦና ውቅሩ የተስተካከለና በመልካም ስብዕና የተገነባ ወጣት ሲባል ቅንነትንና በጎነትን የተላበሰ፣ ጠንካራ እና የሥራ ባህሪ ያለው መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህ ዓይነት ወጣት ምክንያታዊ በመሆን ወገኑንና ሀገሩን የመቀየር አቅም እንዳለው አስረድተዋል።

አስተሳሰቡ የተዛባ የልቦና ውቅሩ በመልካም ሁኔታ ያልተቃኘ ወጣት ለቀጣይ ትውልድ የተሻለች ሀገርን ማስረከብ እንደማይችል ጠቁመው፤ እንደ ሀገር ለመቀጠል አሳሳቢ የሆኑ ሁኔታዎችን የሚፈጥር መሆኑንም አመላክተዋል።

ሀገሪቱን ወደ ተሻለ ምዕራፍና ብልጽግና ለማሸጋገር በሚደረገው ጥረት የወጣቶችን አስተሳሰብ በማልማት የለውጥ ትውልድ ለመፍጠር እየተሠራ ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ የስብዕና ልማት፣ የአስተሳሰብ ለውጥና የልቦና ውቅር የሚያስተካክሉ ሥልጠናዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይገባል ብለዋል።

የብሬክስሩ የቦርድ ሰብሳቢ አቶ ነፃነት ዘነበ በበኩላቸው፤ ፕሮጀክቱ ባለራዕይ፣ ቅን፣ አጋዥ፣ ብቃት ያለውና ባለጸጋ ትውልድ ለሀገር ማፍራትን አላማ አድርጓል ብለዋል።

በፕሮጀክቱ ለ20 ሚሊዮን ወጣቶች ሥልጠና የሚሰጥበት መሆኑን ጠቅሰው፤ ሁለት ሚሊዮን የተለወጡ ወጣቶችን በማፍራት አንድ ሚሊዮን የሥራ ዕድሎችን ለመፍጠር ውጥን መያዙን አመላክተዋል።

ሥልጠናው በመጀመሪያው ዓመት በ13 ከተሞች ላይ ለ10 ሺህ ወጣቶች እንደሚሰጥ ገልጸው፤ ፕሮጀክቱ ለራሳቸው ዋጋ እንዲሰጡ በሥነ ምግባር የታነጹና ሠርቶ መለወጥ የሚችል ወጣት ለማፍራት እንደሚያስችል ገልጸዋል።

# ለሶማሊያ ህልውና የተዋደቀችው...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ ፕሮፌሰር ያዕቆብ አርሳኖ እንደሚናገሩት፤ የዐረብ ሊግ አሁን በዓለም ላይ አሉ ከሚባሉት የአካባቢ ድርጅቶች ቀዳሚው ነው። የተቋቋመው በአውሮፓውያኑ 1945 በመሆኑ ወደ 80ኛ አመቱ እየተጠጋ ነው። የተቋቋመው በሰሜን አፍሪካዋ ግብጽና በመካከለኛው ምሥራቅ በሚገኙት ሳውዲ ዐረቢያና ኢራቅን በመሳሰሉ ሀገሮች ነው። በአጠቃላይ 22 አባል ሀገራት ያሉት ሲሆን ዋና መሥሪያ ቤቱም ግብጽ ካይሮ ነው።

አንድ ወቅት ላይ በካምፕ ዴቪድ ስምምነት ምክንያት ግብጽ ከእሥራኤል ጋር ወግናለች በሚል የዋና መሥሪያ ቤቱ መቀመጫ ለትንሽ ጊዜ ወደ ቱኒዝያ ተዘዋውሮ እንደነበር የሚገልጹት ፕሮፌሰሩ፤ አባላቱ በአብዛኛው ዐረብ ሀገራት ቢሆኑም እንደ ሱዳን፣ ሱማሊያ እና ጂቡቲን የመሳሰሉት ሀገራት ዐረባዊነት ይቀርበናል ብለው ስብስቡን የተቀላቀሉ ናቸው። አልፎ ተርፎ አነስተኛ የቆዳ ስፋት ያላት የደሴቷ ሀገር ኮሞሮስም የዐረብ ሊግ አባል ነች ይላሉ።

ፕሮፌሰር ያዕቆብ እንደሚገልጹት፣ የዐረብ ሊግ ረጅም ጊዜ የኖረ ቢሆንም በአባላቱ መካከል ኅብረት፣ አንድነትና የተግባር ቁርኝት ያላበጀ ድርጅት ነው። ስብስብ ከመሆንና በየአመቱ ስብሰባዎችን ከማድረግ ውጪ በተግባር አባላቱን በመጠበቅና ተገን በመሆን ሥራ አልሠራም።

ኢራቅ በጠፍ ጨረቃ ስትወረር የአባላቱ አንዳንድ ሀገሮች ከወራሪው የአሜሪካን መንግሥት ጋር በውልም በጥቅሻም የሚስማሙ ነበሩ። በውስጣቸው ባለው ቁርሾ የተነሳ ትልቁን የሀገር መወረርን እንኳን በተገቢው መንገድ መዝነው ያላዩ ሀገሮች ያሉበት ስብስብ ነው ሲሉም ያክላሉ።

ሊቢያ ከቀኝና ከግራ ከባድ የሆነ ወረራ ውስጥ ገብታ መሪዋ ሲገደልና ሀገሪቷም ተከፋፍላ በድህነት ስትቆራመት ስብስቡ የፈየደው ነገር አለመኖሩን ያወሱት የፖለቲካ ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ፤ በአጠቃላይ የዐረብ ሊግ ከቅርብም ከሩቅም ሀገራትን አሰባስቦ የሊግ አባላት ናቸው ከማለት በቀር ለውስጥ ጉዳይ፣ ለልማት፣ ለእድገት እንዲሁም መንግሥታቱን ከብጥብጥና ከጭቅጭቅ ለማዳን እና በየጊዜው ከውስጣቸው የሚፈልቀውን ሽብርተኝነትን ለመከላከል አቅም ያጣ ድርጅት ነው ይላሉ።

«የሊጉ መቀመጫ የሆነችው ግብጽ አቅም አልባውን ስብስብ ጥቅሜ ተነካ ባለች ቁጥር አብሯት እንዲያጨበጭብ ታደርገዋለች» በማለት እስካሁን ዋጋ ያለው ሃሳብ ከማቅረብ ይልቅ የግብጽን አቋም ማራገብን የመረጠ ድርጅት መሆኑን ይገልጻሉ።

የዐረብ ሊግ የሦስትዮሽ ስምምነት ላይ ሳይደረስ የዓባይ ግድብ እንዳይሞላ ሲጠይቅ ቆይቷል። ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ እና በዓባይ ግድብ ላይ እየወሰደች ካለችው የተናጠል እርምጃ ትቆጠብ የሚል መግለጫ ሲያንጋጋ ከርሟል። የፀጥታው ምክር ቤት የዓባይ ግድብን አጀንዳ አድርጎ እንዲወያይና ድርድሩ ከአፍሪካ ኅብረት እንዲነጥቅ አራት ሀገራትን በአባልነት ያቀፈ ኮሚቴ አቋቁሞ የፀጥታው ምክር ቤትን ሲወተውትም ነበር። ይህ ሁሉ አልበቃ ብሎት የዓባይ ግድብን ቋሚ አጀንዳ እስከማድረግም ደርሷል።

የኢትዮጵያና ሶማሊያ ጉዳይ በቅርቡ ከሶማሌ ላንድ ጋር በተደረሰው የመግባቢያ ስምምነት ምክንያት ውዝግብ ማስነሳቱን ያነሱት ፕሮፌሰር ያዕቆብ፤ ግብጽ የዐረብ ሊግ አባል የሆነችው ሶማሊያ ስምምነቱን ተቃውማ ኢትዮጵያን መክሰሷን እንደ መልካም አጋጣሚ በመውሰድ፣ በናይል ሸለቆ ውጤታማ ሥራ በመሥራት ያበሳጨቻትን ኢትዮጵያን ለማጥላላት የዲፕሎማሲ ቀለብ አድርጋ እየተጠቀመችበት ትገኛለች ይላሉ።

ኢትዮጵያ ከአብዛኞቹ የዐረብ ሀገሮች ጋር ሰላማዊና ቀጥተኛ የተናጠል የዲፕሎማሲ ግንኙነት እንዳላት አመላክተው፣ ከአባል ሀገራቱ ጋር የታወቀና የከፋ ለወደፊቱ በጠላትነት የሚያፈላልግ ነገር የለም ነው ያሉት።

አያይዘውም ውይይትን ማዕከል በማድረግ ከሀገሮች ጋር ዘላቂ ጥቅም እንዲኖር ለማድረግ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲዋ በጣም መጠንከር አለባት። ስህተቶችም ከተሠሩ ለማረምና ለማስተካከል ጥረት ማድረግ ይኖርባታል። ጥሩ ነገርም ከሠራች ደግሞ ሌሎች እንዲያውቁላት በርትታ መሥራት አለባት ብለዋል።

የታሪክ ተመራማሪው ረዳት ፕሮፌሰር አደም ካሚል በበኩላቸው፤ ዐረብ ሊግ በካይሮ የሚገኝ በግብጽ ቁጥጥር ስር ያለ ድርጅት ነው። ከምስረታው አንስቶ ድርጅቱን የሚመሩት ግብጻውያን ናቸው። ስለዚህ ዐረቦች የግብጽን ፍላጎት ለማሟላት ሲሉ በሚያውቁትም በማያውቁትም እየተጎተቱ ወደ ግብጽ ይሄዳሉ። ሀገሮቹ በአባልነት አሉበት እንጂ በአፈጻጸም ደረጃ ከዜሮ በታች ናቸው ይላሉ።

አሁን በሶማሊያ ጉዳይ የመጡብን የግድቡ ጉዳይ ስላለቀና ምንም ማድረግ ስላልቻሉ ነው የሚሉት ፕሮፌሰሩ፤ በሶማሊያ ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን ያለ የሌለ ኃይሏን ተጠቅማ መስዋትነት የከፈለችው ኢትዮጵያ መሆኗን በመጥቀስ፣ አንድም የግብጽ ወታደር በዚያ አለመሳተፉን ያነሳሉ።

ግብጾች በአሁኑ ሰዓት በሀገራቸው ወደ 4ሺህ የሚጠጋ ሚዲያ እንዳላቸውና በኢትዮጵያ ጉዳይ 42 ጋዜጠኞችን ማሰማራታቸውን የጠቆሙት ፕሮፌሰር አደም፤ «እነሱ እንደፈለጉ ይጬኹ፤ እኛ ሥራችንን ነው መሥራት ያለብን። ይህን ሁሉ የሚያደርጉት ኢትዮጵያ በቀይ ባሕር ላይ ዐሻራ ሊኖራት አይገባም በሚል ነው» ይላሉ።

የዐረብ ሊግ መግለጫ ማውጣቱ ኢትዮጵያን እንደማይጎዳት አመላክተው፤ አሁን የሚያወጡት መግለጫ አያስደነግጥም። ኢትዮጵያ በአፍሪካና በሙስሊሙ ዓለም ትልቅ ቦታ ያላት ሀገር ናት። እነሱ እኛን ሊጎዱን የሚችሉት ራሳችን ጋር ክፍተት ሲያገኙ ነው።

ፕሮፌሰር ያዕቆብ ወደፊትም አልፎ አልፎ በተለያየ ምክንያት ከአባል ሀገሮቹ ጋር የሚነሱ ጭቅጭቆች ሊኖሩ እንደሚችሉ ጠቁመው፤ በሀገሮች መካከል ያሉ ልዩነቶች በሚፈቱበት በተለመደው ዲፕሎማሲያዊ መንገድ የመፍታት ጥረት መቀጠል አለበት። በአጠቃላይ ከዐረብ ሊግም ጋር ቢሆን መልካም ግንኙነት ለመፍጠር ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው ብለዋል።

ረ/ፕሮፌሰር አደም ካሚል በበኩላቸው አንድነትና ጥንካሬ ካለን የዐረብ ሊግ በሶማሊያ ጉዳይ ምንም ማድረግ የሚችልበት ዕድል የለም። በአንጻሩ ኢትዮጵያ በዐረቡ ዓለም አረብኛ ተናጋሪ ዲፕሎማቶችን በመመደብ፤ በዐረቡ ዓለም ምን እየተጻፈና እየተነበበ ነው የሚለው ላይ ጠንክራ በመሥራት የቤት ሥራዋን ከተወጣችው ከዐረብ ሊግም ሆነ ከአባል ሀገራቱ ያላት ግንኙነት ሰላማዊ እንዲሆን ማድረግና ግንኙነቷን ማሻሻል ትችላለች ብለዋል።

# ዜጎች በሀገር ግንባታና በሰላም ጉዳዮች...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በከተማ ደረጃ የተደረገው ውይይትም የሃይማኖት አባቶች ቀድሞ ለሀገር ግንባታ የነበራቸውን ሚና የበለጠ አጠናክረው እንዲቀጥሉ የሚያስችል ነው ብለዋል።

የአራዳ ክፍለ ከተማ የእስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ሼክ ሳላህ ሀሰን ኤብራሂም በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የሃይማኖት ተከታዮች በሀገር ግንባታና በሰላምና ፀጥታ ጉዳዮች ላይ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ሊሠሩ ይገባል።

የሃይማኖት አባቶች የሚያስተላልፉትን ሰላማዊ መልዕክት በመቀበል ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ ጠቁመው፤ ከሌላ አካል ጋር የማያጋጩ ጉዳዮችን በመምረጥ በትብብር መንፈስ መሥራት እንዳለባቸውን አመላክተዋል።

የሃይማኖት አባቶችም በአካባቢያቸው ያልተገባ ድርጊት ሲመለከቱ እንደ አባትነታቸው የሀገርን እሴቶች በጠበቀ መልኩ ሊመክሩና ሊያስተምሩ ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

ከኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስትያናት ህብረት የመጡት ፓስተር ሙላቱ ኤርሚያስ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ እያንዳንዱ ምዕመን መንፈሳዊ ሕይወቱን በማጠናከር ለሀገሩ በርትቶ ሊሠራ ይገባል፤

አብዛኛው ምዕመን የየትኛው ሃይማኖት ተከታይ እንደሆነ ይገልጻል እንጂ ትክክለኛውን የሃይማኖት አስተምሮ ሲከተል አይታይም ያሉት ፓስተር ሙላቱ፤ ምዕመናኑ ትክክለኛውን የሃይማኖት አስተምሮ ተግባራዊ በማድረግ ለሀገር ሰላምና አንድነት መቆም አለበት ብለዋል።



አባ ገብርኤል ወልደዮሐንስ



ሼክ ሳላህ ሀሰን ኤብራሂም

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## አምራች እና ሸማችን ማን ይታደጋቸው?

ዋሰልኝ አየለ

ባለፈው አርብ በማኅበራዊ መገናኛ አውታር አንድ ቪዲዮ ሲዘዋወር አየሁ። በቪዲዮው ላይ አንድ ወጣት ገበሬ ቲማቲም ስንት እንደሚሸጡ ተጠይቆ 3 ብር እየሸጡ እንደሆነ ተመለከትኩ። የተጋነነ ስለመሰለኝ ብዙም አላመንኩም ነበር። ጉዳዩን ለአንድ የሥራ ባልደረባዬ ነገርኩት፤ 3 ብር መሸጡን እርግጠኛ ባይሆንም ገበሬዎች 8 ብር እየሸጡ እንደሆነ ግን ከቤተሰቦቹ እንዳረጋገጠ ነገረኝ።

ሌላም ማሳያ ልጨምር። ባለፈው እሁድ ሌላ ቪዲዮ አየሁ፤ ይህኛው ደግሞ ደላላ ያጠራቀመው ቲማቲም ተበላሽቶ ሲጣል የሚያሳይ ነው። ብዙ ሰዎች ‹‹ተመልከቱ የደላላን ክፋት! በዘይትና በጤፍ የለመዱትን ምርት የመደበቅ ልማድ በቲማቲም እንደግማለን ብለው ተበላሽቶ አከሰራቸው!›› እያሉ ሰዎች በቀልድም በቁም ነገርም አስተያየት ሲሰጡበት ነበር።

ባለፈው ቅዳሜ አዲስ አበባ ውስጥ ቲማቲም ጠየቅኩ፤ ምንም እንኳን ከአካባቢ አካባቢ፣ ከንግድ ቤት ንግድ ቤት ቢለያይም 35 ብር አሉኝ። አምራቾች ግን 3 ብር እየሸጡ ነው። ግዴለም! 3 ብር የተባለው ምናልባት የተጋነነ ሊሆን ይችላል እንበልና 8 ብር የሚሸጡትን እንያዝ። ከአዲስ አበባ 300 ኪሎ ሜትር በማይሞላ ርቀት ውስጥ የሚመረት ምርት በአንድ ኪሎ ብቻ የ27 ብር ልዩነት አለው።

በቀጥታ ገበሬዎች በሚሸጡበት ዋጋ አዲስ አበባ ውስጥ ይሸጥ ማለቴ አይደለም፤ መጓጓዣን ጨምሮ ብዙ ወጪዎች እንዳሉት ግልጽ ነው። ዳሩ ግን ቢያንስ በአንድ ኪሎ ከሦስት እጥፍ በላይ ሲሆን አምራቹም ሸማቹም እየከሰረ መሆኑን ያሳያል።

ብዙው የአዲስ አበባ ነዋሪ ምርት ሲወደድበት ምርት ጠፍቶ ይመስለዋል። ዳሩ ግን ነገሩን የሚያበለሻሸው በመሃል ያለ ደላላ ነው። ቲማቲምን እንደ ማሳያ የወሰድነው ከገጠመኝ ለመነሳት እንጂ በሁሉም የግብርና ምርቶች ተመሳሳይ ችግር ነው ያለው። አምራቹም ሸማቹም እየተጎዱ ነው። በተለይ አምራቹ ገበሬ ላቡን ጠብ አድርጎ አምርቶ አንድ ኪሎ 8 ብር ይሸጣል። የላቡን ዋጋ አያገኝም። ገበሬው ገንዘብ ለማግኘት ያለው ብቸኛ የገቢ ምንጭ ያመረተውን ምርት መሸጥ ነው። ዳሩ ግን ፈጣሪንም ሕግንም የማይፈራ ህሊና ቢስ ደላላ ያጭበረብረዋል። ገበሬውን ‹‹አዲስ አበባ ውስጥ 10 ብር ነው የሚሸጥ›› ሊለው ይችላል። አዲስ አበባ ያለውን ሸማች ደግሞ ‹‹ከገበሬው 20 ብር ነው የማመጣው›› ሊለው ይችላል። የአዲስ አበባ ነዋሪ እና 300 ኪሎ ሜትር በማይሞላ ርቀት ውስጥ ያለ አምራች ገበሬ የማይተዋወቁ፣ የማይገናኙ ነው የሚመስለው።

አምራቹ ገበሬ ዓመቱን ሙሉ የለፋበትን ምርት ሸጦ የሚፈልገውን ጉዳይ መሸፈን አይችልም። በተመሳሳይ በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራው የከተሜው ነዋሪ የሚያገኛትን ገቢ በአንድ ነገር ብቻ ይበትናል። የሀገሩ የጀርባ አጥንት የሆነውን አምራች ገበሬ አመስግኖ እንዳይኖር ደላላ የሚባል ደንቃራ ተጋርጦበታል። እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ የከተሜው ነዋሪ ‹‹ምነው ገበሬዎች እንዲህ ጨከኑ?›› እያለ ሊያማርር ይችላል፤ ገበሬው ከከተሜው ሸማች በላይ እየተጎዳ መሆኑን አያውቅማ!

አንድ ምርት ተወደደ ሲባል የሚመለከተው የመንግሥት ተቋም ‹‹የምርት እጥረት የለም›› የሚል መግለጫ ይሰጣል። ዳሩ ግን ማንም አያምነውም። እውነታው ግን ገበሬው ያመረተውን ምርት በርካሽ ዋጋ ለደላላ እየሸጠ መሆኑ ነው። በእርግጥ አንዳንድ ጊዜ የመንግሥት መግለጫ የማይታመንበት ምክንያት በድለላ ሴራው ውስጥ ራሳቸው የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎችም ስለሚኖሩበት ነው፤ ባይኖሩበት እንኳን ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ስለማያደርጉ ነው። ፍተሻ ተደረገ ተብሎ የተደበቀ ምርት ይገኛል። ይህ በየዓመቱ የተለመደ ነው። ዳሩ ግን የማያዳግም እርምጃ ሲወሰድ እና ዳግም እንዲህ ዓይነት ጥፋት እንዳይሠራ በቂ ክትትል ሲደረግ አይስተዋልም። በዚህም ምክንያት አምራች ገበሬ እና በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራው ሸማች በችግር ይሰቃያሉ፣ አልጠግብ ባይ ደላላ ግን ብቻውን ያጋብሳል።

እንዲህ ዓይነት ድርጊት ከፍተኛ ቁጥጥር ካልተደረገበት የመንግሥትን እና የሀገርን ገጽታ ያበላሻል። በአገልግሎት ዘርፍ የተሰማራው ሸማች በኑሮ ውድነት መንግሥትን እና ሀገሩን ያማርራል፤ አምራች ገበሬውም ምርቱን ሸጦ በገንዘቡ ማግኘት ያለበትን አገልግሎትና የፋብሪካ ምርት መግዛት ስለማይችል እሱም በኑሮ ውድነት መንግሥትን እና ሀገሩን ያማርራል። አምራችም ሸማችም በኑሮ ውድነት ይሰቃያሉ፤ በመሃል ተጠቃሚው ደላላ ብቻ ይሆናል ማለት ነው።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚነት ‹‹ምርትን ከገበሬው›› በሚል ቅዳሜና እሁድ በብዙ የአዲስ አበባ አካባቢዎች የሚከናወን የምርት ሽያጭ ገበያ አለ። ይህ ሊመሰገን የሚገባ እና ብዙዎችን ከአምራቾች ጋር ያገናኘ ነው። ይህ ጥሩ ሆኖ ሳለ፤ ደላሎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ከፍተኛ ቁጥጥር ግን መደረግ አለበት። መንግሥት ደላላን የመቆጣጠር ሥራ ካልሠራ ከኑሮ ውድነት ወቀሳ አይድንም። የኑሮ ውድነትን በድርቅ እና በሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ማሳበብ መንግሥትን ከተወቃሽነት አያድነውም። ምርት ሳይጠፋ ሸማቹም አምራቹም እየተሰቃዩ ሊኖሩ አይገባም።

በነገራችን ላይ ይህ አሁን ያለንበት ወቅት የመኸር ወቅት ነው። የመኸር ወቅት ማለት ደግሞ የግብርና ምርቶች የሚረከሱበት ነው። ዳሩ ግን የግብርና ምርት የረከሰው ለገበሬው ብቻ ነው፤ ሸማቹ ዛሬም በድሮው ዋጋ (እንዲያውም አንዳንዱ ምርት ጨምሮ) ነው እየገዛ ያለው። በርካሽ እየገዛ ያለው ደላላው ብቻ ነው።

ተማሪ እያለሁ ከአምራች ገበሬዎች የሰማሁት አንድ ትዝብት ብዙ ጊዜ ትዝ ይለኛል። ገበሬው ለአንዳንድ ጉዳዮች ከተማ ቦታ ይሄዳል። ምግብ ቤት ገብቶ ምግብ ያዛል። የሆነ ወቅት ላይ ጤፍ ተወደደ ተብሎ የምግብ ዋጋ ይጨምራል። ትንሽ ቆይቶ የጤፍ ዋጋ ይቀንሳል፤ ዳሩ ግን የምግቡ ዋጋ አይቀንስም። ይህን የሚያጋጥመው ገበሬ ጤፉን በርካሽ መሸጡን እያስታወሰ ‹‹ባለፈው ጤፍ ተወዶ ነው አላችሁ፤ ምነው ጤፉ ሲቀንስ እናንተ የማትቀንሱት? እያለ በቀልድም በቁም ነገርም ይናገራል። ‹‹ኸረ ክፉ ቀን አትጥሩ!›› እያሉ ወቀስ ያደርጋሉ።

የገበሬውን ትዝብት አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ማረጋገጥ እንችላለን። የሆነ ወቅት ላይ ቲማቲም ተወደደ ተብሎ (እስከ 80 እና 90 ብር ደርሶ ነበር) የቲማቲም ምግቦች ተወደዱ። እነሆ ዛሬ ከግማሽ በታች ቀንሶ እስከ 35 እየተሸጠ ነው። የቲማቲም ምግቦች ግን በዚያው ዋጋ ናቸው። ሲጨምር ይጨምራሉ፤ ሲቀንስ ግን አይቀንሱም።

ከምንም በላይ ግን ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የደላላ ጉዳይ ነው። ጥቂት ደላላ ብቻ እየተጠቀመ አምራች ገበሬ እና ሸማች ማኅበረሰብ በኑሮ ውድነት ሊሰቃይ አይገባም!

# ዓለም አቀፍ

## ኒው ዮርክ ዩኒቨርሲቲ አንድ ቢሊዮን ዶላር ልገሳ በማግኘቱ በነፃ ሊያስተምር ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር



የአሜሪካው ኒው ዮርክ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ትምህርት ቤት አንድ ቢሊዮን ዶላር ልገሳ ከአንዲት ግለሰብ በማግኘቱ የሕምክና ትምህርት ከክፍያ ነፃ ሊሰጥ ነው።

የቀድሞዋ ፕሮፌሰር እና በሕይወት የሌሉት የዎል ስትሪት ባለሀብት የነበሩት ግለሰብ ሚስት የሆኑት የ93 ዓመቷ ዶክተር ሩት ጎትስማን አንድ ቢሊዮን ዶላር በልገሳ ያበረከቱት በኒው ዮርክ ዩኒቨርሲቲ ለአልበርት አንስታይን የሕክምና ትምህርት ቤት ነው።

ይህም የገንዘብ ልገሳ ለአንድ የአሜሪካ ትምህርት ቤት በታሪክ ከተሰጠ ገንዘብ ከፍተኛው ሲሆን፣ የሕክምናው ትምህርት ቤትም እስካሁን ካገኘው ቀዳሚው ልገሳነው ተብሏል።

የዩኒቨርሲቲው ዲን ዶክተር ያሮን ዮመር ልገሳውን በተመለከተ «ትምህርት ቤታችን መክፈል የሚችሉትን ብቻ ሳይሆን ለተነሳንለት ዓላማ ቁርጠኝነት ያላቸውን ተማሪዎችን ለመሳብ መሠረታዊ ለውጥ ያመጣል» ብለዋል።

በሕክምናው ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች በዓመት ወደ 59 ሺህ ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ መክፈል የሚጠበቅባቸው በመሆኑ በርካቶች ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ለከፍተኛ ዕዳ ይዳረጋሉ።

የሕክምናው ትምህርት ቤት ልገሳውን ማግኘቱን ተከትሎ እንዳሳወቀው የዚህን ዓመት የትምህርት ክፍያ የፈጸሙ ተማሪዎች ገንዘባቸው የሚመለስላቸው ሲሆን፣ ከመጪው ነሐሴ ጀምሮ ደግሞ በነፃ ትምህርታቸውን ይቀጥላሉ።

የገንዘብ ልገሳውን የሰጡት የ93 ዓመቷ ዶክተር ጎትስማን እ.አ.አ. ከ1968 አንስቶ በትምህርት ቤቱ በመምህርነት ያገለገሉ ሲሆን፣ በሙያቸው ባካሄዷቸው ጥናቶች እና ምርምሮች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

በኒውዮርክ ካሉ ባለሀብቶች አንዱ የነበሩት የዶክተሯ ባለቤት ዴቪድ ጎትስማን ያረፉት ባለፈው ዓመት በ96 ዓመታቸው ነበር።

ዶክተር ጎትስማን ከኒው ዮርክ ታይምስ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ባለቤታቸው ከማረፋቸው በፊት ያላቸውን ከፍተኛ መጠን ያለውን ሀብት በሙሉ ወደ እሳቸው ያስተላለፉ ሲሆን በገንዘቡም «ትክክል ነው ያልሽውን ሁሉ አድርጊበት ብሎኛል» በማለት በውርስ ካገኙት ገንዘብ አንድ ቢሊዮን ዶላሩን ለሕክምና ትምህርት ቤቱ አበርክተዋል።

## ከተመረዘ ሽሮፕ ጋር ግንኙነት አላቸው የተባሉ 23 ሰዎች ተፈረደባቸው

በጋዜጣው ሪፖርተር



ለ68 ሕፃናት ሞት ምክንያት ነው ከተባለው የተመረዘ የሳል ሽሮፕ ጋር ግንኙነት አላቸው የተባሉ 23 ሰዎች ኡዝቤክስታን ውስጥ ተፈረደባቸው።

ከመድኃኒቱ ጋር በተያያዘ ተከሰው ፍርድ ቤት የቀረቡት ግለሰቦች ታክስ በማጭበርበር፣ ደረጃውን ያልጠበቀ ወይም ሐሰተኛ መድኃኒት በመሸጥ፣ ኃላፊነትን አላግባብ በመጠቀም፣ በግድየለሽነት፣ ሐሰተኛ ሰነድ በመጠቀም እና ጉቦ በመቀበል ጥፋተኛ ተብለዋል።

ለእነዚህ ጥፋቶችም የኡዝቤክስታን ፍርድ ቤት በተከሳሾቹ ላይ ከሁለት እስከ 20 ዓመት የሚደርስ እስር ፈርዶባቸዋል።

በዋና ከተማዋ ታሽኬንት ባለ ፍርድ ቤት ጉዳዩ በተሰማበት ጊዜ በመርዛማው ሽሮፕ የሞቱት ሕፃናት ቁጥር ቀደም ሲል ከተነገረው ከፍ ብሎ ቀርቧል።

ከስድስት ወራት በፊት ክሱ በተከፈተበት ጊዜ 65 ሕፃናት መሞታቸው የተገለጸ ሲሆን፣ አሁን ግን የሟቾች ቁጥር በሦስት ከፍ ማለቱን ዐቃቤ ሕግ አስታውቋል።

አደገኛ ነው የተባለው የሕፃናት የሳል ሽሮፕ ማሪዮን ባዮቴክ በተባለ የሕንድ ፋብሪካ የተመረተ ሲሆን፣ ኳራማክስ ሜዲካል የተባለው ድርጅት ደግሞ ኡዝቤክስታን ውስጥ ለተጠቃሚዎች አሰራጭቷል።

ረጅሙ የ20 ዓመት የፍርድ ቤቱ የእስር ቅጣት የተላለፈውም የመድኃኒቱ አከፋፋይ በሆነው ኩባንያ ዋና ዳይሬክተር ላይ መሆኑ ታውቋል።

ሮይተርስ የዜና ወኪል እንደዘገበው ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ መድኃኒቶች ፈቃድ የሚሰጠው የመንግሥት ተቋም ከፍተኛ ባለሥልጣንም የበርካታ ዓመታት የእስር ቅጣት ተፈርዶበታል።

ኡዝቤክስታን ውስጥ መድኃኒቶቹን የተጠቀሙ የ18 ሕፃናት ሕይወት ካለፈ በኋላ የዓለም ጤና ድርጅት በሕንዱ ማሪዮን ባዮቴክ የሚመረቱ ሁለት ሽሮፖች «ከደረጃ በታች ናቸው» ብሎ አስታውቋል።

ድርጅቱ እንዳለው አምብሮኖል እና ዶክ-1 ማክስ የተባሉት ሁለት ሽሮፖች ከሚጠበቀው መጠን በላይ አደገኛ ንጥረ ነገሮች በውስጣቸው ይዘዋል።

በወቅቱ የመድኃኒቶቹ አምራች ማሪዮን ባዮቴክ የቀረበውን ክስ በማስተባበል ለቢቢሲ በሰጠው ምላሽ፣ በዓለም ጤና ድርጅት ግኝት «እንደማይስማማ» አሳውቆ ነበር።

ነገር ግን የሕንድ ጤና ሚኒስቴር የመድኃኒቶቹ ምርት እንዲቋረጥ ያደረገ ሲሆን፣ አምራቹ ያለበት የኡታር ፕራዲሽ ግዛት የምግብ ደኅንነት ባለሥልጣን ደግሞ የፋብሪካውን ፈቃድ ካገደው በኋላ መጨረሻ ላይ «አስከወዲያኛው» ሰርዞታል።

የኡዝቤክስታን ፍርድ ቤት በተከሳሾቹ ላይ እስር ከመበየኑ በተጨማሪ በሳል ሽሮፑ ምክንያት ሕይወታቸው ላለፈው የ68ቱ ሕፃናት ቤተሰቦችና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ሕፃናት ቤተሰቦች ለእያንዳንዳቸው የ80 ሺህ ዶላር ካሳ እንዲከፈላቸው ወስኗል።

## ነፃ ሃሳብ

# አድዋ - የጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ችቦ

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ..የአባቶቼ መልክና ቀለም የቀለመኝ። በኢትዮጵያዊነቴ ውስጥ እውነት ናቸው ብዬ ከተቀበልኳቸውና ባስታወስኳቸው ቁጥር ከሚያስደንቁኝ እውነቶች ውስጥ አንዱ የአድዋ ታሪክ ነው። አድዋ የጋራ መደነቂያችን እንደሆነ ባምንም እንደእኔ የሚደነቅበት ስለመኖሩ ግን እጠራጠራለው። ከእውነቴ አንዱን ለማንሳት ያህል አድዋ ለኔ በዓለም ታሪክ፣ በሰው ልጅችም ስልጣኔ ያልተደረሰ፣ እውነት በማይመስል ታሪክ ውስጥ ነጻነት የተጻፈበት የሰው ልጆች ሁሉ የቀና ማለት መለኮት ነው።

ለሰው ልጆችም አስደማሚ የነጻነት ገድል ታሪክ ባለቤቶች ነን። ይሄ ገድል ከአባቶቻችን ወደእኛ እንዴት መጣ፣ ዓለምንስ እንዴት አስደመመ ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ አብሮነትን ነው። አብሮነት ከኃይልና ከብርታት ባለፈ በየትኛውም ዘመን የሀገርና የሉአላዊነት ዳር ድንበር ማስከበሪያ ነው። አድዋ በየትኛውም ምሁራን አንደበት ቢተነተን ይሄን መሳዩን እውነታ ነው የሚፈነጥቅልን። በአባቶቻችን ስልጣኔና ዘመናዊነት እንዲሁም ደግሞ በከባድ መሳሪያ የመጣ ሳይሆን በአንድነትና በወንድማማችነት መንፈስ የመጣ ነው።

ይሄ የአይበገሬነት መንፈስ መቶ ዓመታትን ተሻግሮ እንኳን ቀለሙ ዛሬም አልደበዘዘም። ከሀገር ፍቅርና ከኢትዮጵያዊነት ውጪ ምንም የማይስተዋልበት ያ የአድዋ ዘመን እኔንና እናተን ሲፈጥር መነሻው ሀገርና ሕዝብ ነበር። ክብርና ነጻነት፣ ሉአላዊነትና አትንኩኝ ባይነት ነበር።

እንደ አድዋ ያለ ዘመን ተሻጋሪ ታላላቅ ታሪኮች ደምቀው የሚታዩት ሕብረት በወለደው ሕዝባዊነት ውስጥ ነው። አድዋን ሻማ አብርቶ፣ ጀግኖቻችንን አስታውሶ ማለፍ ብቻውን ዋጋ አይኖረውም። መንፈሳቸውን ወርሰን፣ እምነትና ጽናታቸው ተጋብቶብን አሁን ካለንበት የቡዳኔ ልክፍት ወጥተን በሕብረብሄራዊነት ስንቆም ነው። ዝክረ አድዋ ዝክረ ኢትዮጵያ፣ ዝክረ አፍሪካ፣ ዝክረ ጥቁርነት ነው። ትርጉም ያለው እንዲሆን ትርጉም ባለው ሀገራዊ አስተሳሰብ ስር መሰባሰብ ያስፈልጋል።

ዛሬም ድረስ ኢትዮጵያዊነትን ባስቀደሙ በአባቶቻችን ታሪክ የምንጠራ ነን። ታሪክ መዘን እንዲህ ነበርን ብለን የምንኮፈስ። አድዋ ሊያስተምረን የሚችለው ትልቁ ነገር አንድነት በዋጀው ወንድማማችነት ሀገራዊ እና ቀጠናዊ፣ ዓለም አቀፋዊ ድሎችንም መቀዳጀት ነው። ታሪክ ማውራት ብቻውን አንድን ሀገር ወደፊት አያራምደውም። በእኛ ጊዜ ላይ ዳግማዊ አድዋን የሚፈጥር ልዕለ ሰብ መገንባት ድርሻችን ይሆናል።

ታሪክን በዘመን ስናሰላው መነሻና መድረሻው በዛን ሰሞን ይሆናል። ከመጀመሪያው አድዋ እስከ ሁለተኛው የጣሊያን ወረራ ድረስ አርባ ዓመታት በመሀል አሉ። አባቶቻችን ሁለተኛውን የጣሊያን እብሪት ለማብረድ አርባ ዓመት ነው የበቃቸው። ጣሊያን ከዛ ቀድሞ ቢመጣም የማሸነፍና የመመከት ሙሉ ልዕልና ነበራቸው። ለዚህ ምክንያት ሆኖ ከፊት የሚመጣው ደግሞ የሀገር ፍቅርና የነጻነት ጥያቄ ነው።

በአርባ ዓመታት ውስጥ ሁለት አይነት ድሎችን መቀዳጀት ትርጉሙ በምን እንደሚለካ ዛሬም ድረስ አልመጣልኝም። አባቶቻችን በጽኑ ተጋድሎ ሀገር ሲጠብቁና ሉአላዊነትን ሲያውጁ ኖረው ያለፉ ናቸው። እኔና እናንተ ግን መቶ ዓመታት አልፈውን ዛሬም ድረስ በአባቶቻችን የትላንት ታሪክ የምንጠራ ነን። የእኛ አድዋ የታለ? የእኛ አድዋ መቼ ነው የሚጀምረው? መቼ ነው በድህነት ላይ ታሪክ የምንሰራው?

ኅጠኝነት አድዋችንን ሰውሮብናል። በዘርና በኅሳ መቧደናችን ልዕልናችንን ሸሽጎብናል። ከዚህ አስተሳሰብ እስካልወጣን ድረስ የእኛን አድዋ አንደርስበትም። በልባችን ላይ ከትዕቢታችን ቀድማ፣ ከጥላቻችን ቀድማ ኢትዮጵያ ካልመጣች አደጋ ላይ ነን። ከብሔራችን ቀድሞ በነፍሳችን ላይ ኢትዮጵያዊነት ካልነገሰ ታሪክ ከማውራት ባለፈ ታሪክ መስራት አይቻለንም።

የአባቶቻችን አድዋ በኢትዮጵያዊነት ጀምሮ በኢትዮጵያዊነት ያበቃ ነው። የእኛ ታሪክ ግን በእኔነት ጀምሮ በራስወዳድነት ያበቃ ነው። ብሄርተኝነት ከኢትዮጵያዊነት ቀድሞ ደማማቅ ጳዳሎቻችንን አደብዝዞብናል። ጥንተ ከፍታዎቻችን አቧራቸው ረግፎ አንቱታን እንዲያገኙ በዚህ ትውልድ ላይ ኢትዮጵያዊነት ሊለመልም ግድ ይላል።

አድዋ ኢትዮጵያዊነት ቀድሞ ኢትዮጵያዊነት በተከተለበት የወንድማማችነት መንፈስ የተፈጠረ ነው። እንደሀገር የተጀመሩ ብዙ እድሎች አሉን። በማለቅ ላይ ያሉ ትንሳኤ አብሳሪ ጸጋዎች አሉን። እኚህ ሁሉ ወደመሆን እንዲመጡ ለሀገራችን ምቹ የሆነ ተግባቦትና ምክክር ያለበት ፖለቲካዊ ምህዳር ያስፈልገናል።

በጠበበ ፖለቲካ የሰፋ ሀገር ትርጉም የለውም። በሰፋ ፖለቲካ ነው የጠበበ ሀገር የሚገዝፈው። ችግሩ ከሀገራችን ሳይሆን ካለፍንበትና እያለፍንበት ካለው የፖለቲካ ምህዳር ነው። እንደ ፖለቲከኛ ከሰፋን፣ እንደ ሕዝብ ከገዘፍን እንደሀገር የማንበረታበት ምንም ምክንያት የለም። አድዋ የሰፋና የገዘፉ ልቦች ነጸብራቅ ነው።

ይሄ ነጸብራቅም ሀገር አድምቆ አፍሪካ ላይ ተንጸባርቋል። ዓለም ላይ መልህቁን ጥሏል። የፖለቲካ ስፋት..የማኅበረሰብ ግዝፈት ማለት ይሄ ነው። የአባቶቻችን ግዝፈት ነው ጠባቧን ዓለም ያገዘፋት። በአድዋ ማግስት መግዘፍ እንጂ ታሪክ እያወሩ ነበርን መዘከር ትርጉም የለውም።

ከልዩነታችን ሀገራችንን ማስቀደም አለብን። የእኛ አድዋ በዚህ መንገድ ካልሆነ በምንም አይፈጠርም። ዛሬም ድረስ የአድዋ ድል ሚስጥሩ ያልገባቸው አሉ፤ ከዚህ የተነሳ ስለድሉ ምርምር ላይ ናቸው። አንዲት ድሃና ኋላቀር ሀገር፣ ምድር የስልጣኔ ፈርቀዳጅዋን ጣሊያንን ልታሸንፍ ቻለች? በሚል ትካዜ ላይ ናቸው። አድዋ ለእኛ ለጥቁሮች ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ኩራት ነው። የዛኑ ያህል ድሉ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ የቁጭትና የውርደት ታሪክ የሆነባቸውም አሉ።

ከአድዋ በፊትና ከአድዋ በኋላ ዓለም ሁለት አይነት ናት። ከአድዋ በፊት ያለችው ዓለም ስለ ጥቁር ሕዝቦች ያላት ምልከታ ሙሉ በሙሉ የተበላሸና ከከሰብአዊ እሳቤ የራቀ ነው፤ ከአድዋ በኋላ ግን ይህ እሳቤ የተገራበት እውነታ ተፈጥራል። ድሉ ለመላው ጥቁር ሕዝብ የነጻነትና የቀና ማለት መለኮት ሆኖ በዓለም አደባባይ ተሰምቷል። አድዋ ለዓለም ጭቁኖች የትንሳኤ ቀን ነው። አድዋ ለዓለም ጥቁሮች የአቢዮት ማግስት ነው።

አሁን ከዚህ የታሪክ ትርክት የሚቀዳ አዲስ አድዋ አዲስ ታሪክ ያስፈልገናል። ደጋግመን ከምናወራው የአባቶቻችን ታሪክ ወጥተን የራሳችንን አድዋ የምንሰራበት ጊዜ ላይ ነን። ከአባቶቻችን ጽናትንና አንድነትን፣ ኢትዮጵያዊነትንም ወስደን በዘርና በኅሳ የቆሸሸችውን ኢትዮጵያ እንደ አዲስ መማገር አለብን። ካለፈው ዘመን ፍቅርና ወንድማማችነትን ወርሰን በጥላቻና በመለያየት የቆመችውን ሀገራችንን መሰብሰብ አለብን። አድዋን ስንዘክረው መቶ ሀያ ስምንት ዓመት ሆነናል እርግጥ አድዋ ማብቂያ የለውም። ከሰው ልጆች ጋር፣ ከነጻነትና ከክብር ጋር፣ ከሰብዐዊነትና ከጥቁርነት ጋር አብሮ የሚነሳ ገድል ነው።

ከአባቶቻችን እንደተቀበልነው ሁሉ ለልጆቻችን የምናወርሳቸው ሌላ አድዋ ያስፈልገናል። መጪው ትውልድ የአባቶቹንና የአያቶቹን ጥንድ አድዋ እንዲያከብር ዛሬ የእኔና የእናንተን አድዋ መፍጠር አለብን። በድህነትና በኋላቀርነት ላይ፣ በዘረኝነትና በጥላቻ ላይ፣ በጦርነትና በመገፋፋት ላይ አዲስ አድዋ ያስፈልገናል። ሰላምን በመስበክ፣ አንድነትን በማጠንከር፣ በልማትና በእድገት ላይ አዲስ ታሪክ ያሻናል።

ታሪክ ተዐምር አይደለም የሚፈጠረው በፍቅር ነው። ታሪክ የሚጻፈው በአንድነት ነው። ፍቅር ውስጥ የቆሙ ነፍሶች ሁሉ ባለታሪክ ናቸው። በአንድነትና በይቅርታ ውስጥ የጸኑ ልቦች እነሱ የታሪክና የታዐምር ባለቤቶች ናቸው። ታሪካችንን የሰወርነው ብሄር ተኮር እሳቤን ባነገበ ፖለቲካና ፖለቲከኞች ነው። እድላችንን የደበቅነው ፍቅርን በማያውቅ ጨለማ ልባችን ነው። ዳግማዊ አድዋን ለመፍጠር እንደአባቶቻችን መሆን አለብን።

ዓላማቸውን ወርሰን፣ ሕልማቸውን ተጋርተን በቀናው ጎዳና ላይ መቆም ያዋጣናል። እነሱ የኖሩት ለኢትዮጵያ ነበር የሞቱትም ለኢትዮጵያ ነው። እነሱ ቋንቋቸው አንድነት ነበር በአንድነትም አድዋን ፈጥረው አልፈዋል። የእኛ ቋንቋ ምንድነው፤ እውቀታችንስ ? እኛ ቋንቃችን ተደበላልቋል፤ እውቀታችንም በእኔነት ረክሷል። ተነጋግረን መግባባት ተስኖናል። ከዚህ የተነሳም ለራሳችን ኖረን ለራሳችን መብቃት ያልቻልነው። ለዚህ እኮ ነው አድዋን መሳይ ታሪክ ያልሰራነው። ለዚህም እኮ ነው የምንናፍቃትን ኢትዮጵያ አምጠን መውለድ ያልቻልነው።

ምኞት ተግባር ካልታከለበት ከንቱ ልፋት ነው። በምኞታችን ውስጥ ሆና ልናያት የምንፈልጋት ሀገር አለችን፤ በሀሳባችን ውስጥ ሆኖ እንድናየው የምንፈልገው ሕዝብ አለን። ተግባራችን ግን ሌላ ነው.. ጥላቻና ዘረኝነት የሞላው። እኔነትና ራስወዳድነትን የቀላቀለ። በዚህ ማህጸን ውስጥ አድዋ አይኖርም መቼም ቢሆን የለም። ይሄ ማህጸን የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ አምጦ መውለድ አይቻለውም።

ማህጸን ሀሳብ ነው..ማህጸን ምግባር ነው። ማህጸን ፍቅርና አንድነት፣ ይቅርታና ወንድማማችነት ያሉበት ስፍራ ነው። ማህጸን እውነትና ፍትህ፣ እኛነትና ኢትዮጵያዊነት የሚፈጠሩበት ለምለም ቦታ ነው። በዚህ ማህጸን ካልሆነ አድዋንም ሆነ የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ አንደርስባቸውም። ማህጸናችን ጥላቻን ጸንሶ ጥላቻን መውለዱ ይብቃው። ማህጸናችን እልኸኝነትን ጸንሶ እልኸኝነትን መውለዱ ይቁም።

ለመነጋገርና ለመግባባት፣ ለመተቃቀፍና አንተ ትብስ አንቺ ለመባባል የሚሆን ማህጸን ያስፈልገናል። አድዋ በዛ ውስጥ ነው።

አድዋ አጥቢያ ነው..የኢትዮጵያዊነት የአንድነትና የነጻነት ዜማ የሚደመጥበት። የጽናት፣ የሉአላዊነት ቅኔ መወድስ የሚሰማበት..የክብር፣ የሕብር..ደብር። አድዋ ታቦት ነው ኢትዮጵያዊነት የተቀረጸበት የብኩርና ጽላት። ሞት የዋጀው፣ ጉስቁልና ያረታው የማንነት አውድ። አድዋ ዋርካ ነው የኩራት፣ የክብርና የትህትና የነጻነትም የመምሬ አድባር።

አድዋ ተራራ ነው..ትልቅና ጥልቅ የኢትዮጵያዊነት ስጋና ደም። ጽናት እምነትና አሸናፊነት የከተቡት። አድዋ ጌጥ ነው..የመቶ ሀያ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን አሸክታብ። የሰማኒያና ከዛ በላይ ብሔረሰብ የኩራትና የልዕልና ምንጭ። የመላው ጥቁር ሕዝብ መታበያ..መመጻደቂያ። አድዋ ይሄን ሁሉ ነው.. እኛም ይሄን ሁሉ ነን።

አድዋን የፈጠሩ እነዛ ሻከራ እጆች፤ እነዛ ባዶ እግሮች፤ እነዛ ለነጻነት ቀናኢ ነፍሶች ክብር ይግባቸው። ዛሬ አንዲህ ደምቆ ያየነው በነሱ ነው። እነዛ ለነጻነት ቀናኢ ነፍሶች መስዋዕት ባይሆኑ ባይሞቱልንና ኖሮ እኔም እኔን እናተም እናተን ባልሆንን ነበር። ክብር ይግባቸው ሞተው ያቆሙን እነዛ ነፍሶች።

አድዋ የኢትዮጵያዊነት ቀለም ነው..እንደ አፍሪካ ከፊት የቆምነው፣ እንደ ጥቁር ፊተኝነትን ያገኘነው በዚህ እውነት ላይ ተረማምደን ነው። ኢትዮጵያዊነት ነፃነትን በብዙ መስዋዕትነት አምጦ የወለደ ማህጸን ነው። ኢትዮጵያዊነት የዓለምን ታሪክ የቀየረ ነው።

አድዋ በየትኛውም ዘመን ለሚፈጠር ትውልድ መደነቂያና መገረሚያ ነው። ትውልዱ የአባቶቹን አድዋ እያስቀጠለ የራሱን አድዋ ለመፍጠር ከመቼውም ጊዜ በላይ አሁን መነቃቃት አለበት። በአባቶቻችን አድዋ ውስጥ የራሱን አድዋ ለማየት እንደአባቶቹ ያለ ብርቱ አንድነትና ዓላማ ጽናት ያስፈልገዋል። ቸር ሰንብቱ።

**ማህጸን ሀሳብ ነው.. ማህጸን ምግባር ነው። ማህጸን ፍቅርና አንድነት፣ ይቅርታና ወንድማማችነት ያሉበት ስፍራ ነው። ማህጸን እውነትና ፍትህ፣ እኛነትና ኢትዮጵያዊነት የሚፈጠሩበት ለምለም ቦታ ነው። በዚህ ማህጸን ካልሆነ አድዋንም ሆነ የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ አንደርስባቸውም። ማህጸናችን ጥላቻን ጸንሶ ጥላቻን መውለዱ ይብቃው። ማህጸናችን እልኸኝነትን ጸንሶ እልኸኝነትን መውለዱ ይቁም**

# ብዙ ሥራ የሚጠብቀው የቆዳ ኢንዱስትሪ



**ቃልኪዳን አሳዬ**

ኢትዮጵያ በቀንድ ከብት ብዛት ከአፍሪካ ቀዳሚ ስለመሆኗ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ታዲያ ከአፍሪካ ቀዳሚ በሆነችበት የቀንድ ከብት ሃብቷ እምብዛም ተጠቃሚ ስትሆን አይስተዋልም፡፡ በተለይም ከቀንድ ከብቶቿ የምታገኘውን ቆዳ በአግባቡ ጥቅም ላይ አይውልም። አሁን ላይ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ጉልህ ፋይዳ ያለው የቆዳ ኢንዱስትሪ ውለታው የተዘነጋ ይመስላል፡፡ ለዚህም በየጥጋጥጉ የሚጣለው ቆዳ ምስክር ሆኖ ይታያል፡፡

በቆዳ ኢንዱስትሪው ዘርፍ በሚስተዋሉ ውስብስብ ችግሮች ምክንያት ቆዳ ለኢንዱስትሪዎች በአግባቡና ጥራቱን በጠበቀ መንገድ መድረስ አለመቻሉ የዘርፉ ዋነኛ ማነቆ እንደሆነ ይነገራል፡፡ በጥራት ከማዘጋጀት ጀምሮ በተለያዩ ችግሮች እየተፈተነ ያለው የቆዳ ዘርፍ የውጭ ምንዛሪ በማምጣት የአገር ኢኮኖሚን መደገፍ የሚችል ዘርፍ ቢሆንም በተጋረጠበት ውስብስብ ችግሮች ምክንያት ኢንዱስትሪዎች ቆዳን ከውጭ እስከማስገባት የደረሱበት ጊዜ ስለመኖሩ ይነገራል፡፡

የኢትዮጵያ ቆዳ ጥራት ያለው፣ በዓለም የታወቀና ተፈላጊ ቢሆንም፤ አሁን ባለው ሁኔታ ዘርፉ በእጅጉ ተቀዛቅዟል፡፡ ይህም መንግሥትን ጨምሮ በዘርፉ የተሰማሩ ባለድርሻ አካላትን እንዲሁም የአገርን ኢኮኖሚ በብርቱ እየጎዳ ነው፡፡ የቆዳ ኢንዱስትሪው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያጋጠመውን ችግር መፍታት እንዲችልም በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ መቆየታቸው ይታወሳል። መንግሥትን ጨምሮ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ለዘርፉ ትኩረት እንዲሰጡ እየተጠየቀ ባለበት በዚህ ጊዜም በዘርፉ የተሰማሩ ባለሙያዎች የቆዳ ኢንዱስትሪውን ለማነቃቃት ጥረት እያደረጉ እንደሆነ ነው የተገለጸው።

የዝግጅት ክፍላችንም በቆዳ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ዋነኛ ማነቆ የሆኑ ችግሮች ምን እንደሆኑ፤ መፍትሄዎቹ፤ እንዲሁም በቀጣይ ዘርፉን ለማነቃቃት እየተሠሩ ያሉ ሥራዎችን በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር የስጋ፣ ቆዳና ሌጦ ዘርፍ ኃላፊ ከሆኑት አቶ አስመላሽ በርሄ ጋር ቆይታ አድርጓል፡፡

አቶ አስመላሽ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ በየዓመቱ ከዳልጋ ከብቶች ማለትም ከፍየልና ከበግ 31 ነጥብ አንድ ሚሊዮን የሚደርስ ጥሬ ቆዳና ሌጦ ምርት ታገኛለች፡፡ ከዚህ ውስጥም 19 ሚሊዮን ያህሉ ቆዳና ሌጦ አገልግሎት ላይ አይውልም፡፡ ይህ ምርት ወደ ገበያ መግባት ባለመቻሉም በአገሪቷ የውጭ ምንዛሪ ግኝት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ 19 ሚሊዮን ያህሉ ቆዳና ሌጦ አገልግሎት ላይ ቢውል ለሀገሪቱ ከሚያስገኘው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በተጨማሪ የተለያዩ የሥራ ዕድሎችን ለዜጎች መፍጠር ያስችላል፡፡

ነገር ግን ዜጎች ለቆዳ ኢንዱስትሪው ባላቸው የግንዛቤ ማነስ የተነሳ አገሪቷ ከዘርፉ ተጠቃሚ መሆን አልቻለችም። የቆዳ ኢንዱስትሪ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ አንጻር ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘቱ ቆዳ በየቱቦውና በየመንገዱ ተጥሎ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ በአሁን ወቅትም የዘርፉን ችግር በመቅረፍ ሀገሪቷ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው።

‹‹በግብይት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ችግሮችን በመፈተሽ ለእያንዳንዱ ችግር መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል›› ያሉት አቶ አስመላሽ፤ በተለይም ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ የዘር ችግሮችን በመለየት የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ ወደ ሥራ ከተገባ ለችግሩ መፍትሔ እንደሚመጣ ነው ያመላከቱት፡፡

ለዘርፉ ዕድገት ማነቆ የሆኑ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት የመፍትሔ አቅጣጫ ለመስጠት በፌዴራል ደረጃ እየተሠራ እንደሆነ የጠቀሱት አቶ አስመላሽ፤ ከንግድና ኢንዱስትሪ እንዲሁም ከግብርና ሚኒስቴር የጥናት ቡድን ተዋቅሮ ከጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢና ከሌዘር አምራቾች ማኅበራት ጋር ጥናት እየተከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ በጥናቱም እንደ ሀገር በሥራ ላይ ከነበሩ ሰባት ሺህ የጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢ ማኅበራት መካከልም አንድ ሺህ ማኅበራት በዘርፉ ባሉ ችግሮች ምክንያት ከገበያ መውጣታቸው ተመላክቷል ነው ያሉት፡፡ ማኅበራቱን ወደ ቀድሞ ሥራቸው በመመለስ ዘርፉን ማነቃቃት የሚያስችሉ ጅምር ተግባራት መኖሩንም ጠቁመዋል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የግብርና ሚኒስቴር ዘርፉን መደገፍና ማልማት የሚጠበቅበት ሲሆን፤ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርም በበኩሉ የገበያ ስርዓቱን በማሻሻል ረገድ የድርሻቸውን ይወጣል ያሉት አቶ አስመላሽ፤ ምርቱን ተቀብሎ ለውጭ ገበያ የማቅረብ፣ የፋብሪካዎችን አቅም የመገንባት፣ የፖሊስ ማሻሻያ እንዲደረግ ግፊት መፍጠርና ሌሎች ስልታዊ ጉዳዮችን ቀርጾ የኤክስፖርት አቅምን የማሳደግ ድርሻ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መሆኑን ነው ያስረዱት ።

በተለይም ገበያው በግብይት ስርዓት መመራት እንዳለበትና ለዘርፉ አስፈላጊ የሆኑ አዋጆችና መመሪያዎች ወደመሬት ወርደው ተግባራዊ መሆን እንዳለባቸው ሲያስረዱ፤ ‹‹ገበያው ለሁሉም ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ተደራሽ መሆን ሲችል የተሻለ ምርት ያለው የተሻለ ዋጋ ያገኛል›› ነው ያሉት፡፡

ዘርፉ እየተነቃቃ በሚሄድበት ወቅት ሀገሪቷ በዓለም አቀፍ ገበያ ከፍተኛ ድርሻ ይኖራታል ያሉት አቶ አስመላሽ፤ አቅራቢዎችም የተሻለ ቆዳ የማምረት ፍላጎታቸው እንደሚጨምርና በግብይት ሰንሰለት ውስጥ ያሉ ተዋናዮችም አስፈላጊውን ጥረት በማድረግ የምርቱ ጥራት እየተሻሻለ የሚሄድ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ ለዚህም የግንዛቤ ማስጨበጫና የማስተዋወቅ ሥራ ከመሥራት ባሻገር ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊወጣ ይገባል በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በቆዳና ሌጦ ምርትና ግብይት ላይ ጥናት ያደረጉት ከፍተኛ ተመራማሪ ዶክተር ረሂማ ሙሰማ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ቆዳና ሌጦ ምርቶች የራሳቸው መለያ ያላቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ የኢትዮጵያ ቆዳ በዓለም አቀፍ ገበያ ተፈላጊ ቢሆንም ለውጭ ገበያ የሚቀርበው የምርት መጠን እየቀነሰ መምጣቱን ነው የተናገሩት፡፡ ይህም ሀገሪቱ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን የገቢ መጠን ማግኘት እንዳትችል አድርጓታልም ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት ከዓለም አምስተኛ ከአፍሪካ የመጀመሪያውን ደረጃ ብትይዝም በአሁን ወቅት ቆዳ በየአካባቢው እንደ አልባሌ ነገር እየተጣለ ይገኛል በማለት የገለጹት ተመራማሪዋ፤ ጥናቱ በዋናነት የተከናወነው በቆዳው ዘርፍ የሚስተዋሉ የችግሮች መነሻ ምክንያታቸውን ለመለየትና የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ለማመላከት እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ቆዳና ሌጦ 80 በመቶው ከአርሶ አደሩ አካባቢ የሚመጣ ሲሆን የተቀረው 20 በመቶው ብቻ በከተማ በሚገኙ ቄራዎች የሚቀርብ በመሆኑ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የጥሬ ቆዳ ሌጦ ምርት እየቀነሰ እንደሚገኝ ተመራማሪዋ አስረድተዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ የቆዳ ፋብሪካዎች 60 በመቶ ያህሉን ቆዳ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ ቢሆንም ጥራቱን የጠበቀ የቆዳ አቅርቦት ማግኘት አልቻሉም፡፡ ይህም በሥራቸው ላይ እንቅፋት እየፈጠረ በመሆኑ ቅሬታ እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡ ስለሆነም ይህን በሚገባ የሚያስተሳስር ሥራ መሰራት ያስፈልጋል፡፡ በተለይም አንድ አንድ የመንግሥት ፖሊሲዎች የቆዳ አቅርቦት ጥራት እንዲቀንስ ካደረጉ ምክንያቶች ውስጥ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ከሌሎች ሀገራት አንጻር ሲታይ የኢትዮጵያ ቆዳና ሌጦ ምርት እየቀነሰ መሆኑ በኢኮኖሚው ላይ ጫና አሳድሯል፡፡ ይሁንና በዘርፉ የሚስተዋሉ ችግሮችን መቅረፍ ከተቻለና ሀገሪቱ ያላትን በቂ ሀብትና የሰው ኃይል በአግባቡ መጠቀም ከቻለች ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቷን ማረጋገጥ ትችላለች፡፡ ከዚህ አንጻር ዘርፉ

**ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብት ከዓለም አምስተኛ ከአፍሪካ የመጀመሪያውን ደረጃ ብትይዝም በአሁን ወቅት ቆዳ በየአካባቢው እንደ አልባሌ ነገር እየተጣለ ይገኛል**

ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ቀደም ባሉ ጊዜያት ለዘርፉ የተሻለ ትኩረት ይሰጥ እንደነበር ያነሱት ዶክተር ረሂማ፤ በአሁን ወቅት ለዘርፉ ያለው አመለካከት አናሳ መሆን፣ ባህላዊ የዕርድ ስርዓት፣ ለሀገር ውስጥ የቆዳ ምርቶች የዜጎች ፍላጎት ማነስ፣ ግልጽ የገበያ ትስስር አለመኖርና ሌሎች በዘርፉ ላይ የሚታዩ ውስንነቶች ስለመኖራቸው አመላክተዋል፡፡

የምርት ጥራት ችግሮችን መፍታት፣ በዘርፉ ለሚገኙ ባለሙያዎች በቂ ስልጠና መስጠት፣ የገበያ ስርዓቱን ማሻሻልና ማዘመን፣ ለዘርፉ ተቋማት አስፈላጊ ድጋፎችን መስጠት፣ ለዘርፉ ማነቆ የሆኑ ጉዳዮችን በየወቅቱ በመፈተሽ መፍትሔ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነም ተናግረዋል፡፡

በቆዳ ኢንዱስትሪው ከ30 ዓመታት በላይ የሰሩት አቶ ከበደ አህመድ በበኩላቸው፤ የቆዳና ሌጦ ዘርፍ በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ወቅት የስጋ ቦርድ በባለቤትነት ይዞ ይሠራበት እንደነበር አስታውሰው፤ ቀጥሎም የጥሬ ቆዳና ሌጦ ልማት ድርጅት እንዲሁም የቆዳና ጫማ ኮርፖሬሽን የሚባሉ ተቋማት በባለቤትነት መርተውታል፡፡ እነዚህ ተቋማት በወቅቱ ዘርፉን መቀየር ቢችሉም ተቋማቱ መቀጠል ሳይችሉ ቀርተው ከፈረሱበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን እነሱን ሊተካ የሚችልና ሙሉ ቁመና ያለው ተቋም አልተፈጠረም፡፡ በዚህ የተነሳ ዘርፉ ሊዳከም ችሏል፡፡

ስለዚህ ጥሬ ቆዳና ሌጦ በየቦታው የሚወድቅበትን ምክንያት በመለየት ችግሩን መፍታት ያስፈልጋል ያሉት አቶ ከበደ፤ በተለይም በቆዳ አሰባሰብና ጥራት ላይ የሚሰራ አካል እንደሚያስፈልግ ጠቅሰው፤ ይህን ማድረግ ሲቻል ቆዳ በአግባቡና በጥራት መሰብሰብ እንደሚችል ተናግረዋል፡፡ አያይዘውም በዓመት ከ40 ሚሊዮን በላይ ጥሬ ቆዳና ሌጦ መሰብሰብ እየተቻለ ነገር ግን ከ50 በመቶ በታች እየተሰበሰበ መሆኑን ገልጸው፤ ይህም በዘርፉ ያሉ ተቋማትና የሚመለከታቸው አካላት በመዳከማቸው ነው ብለዋል፡፡ ለዚህም በዘርፉ ተሰማርተው ከነበሩና 15 ከሚደርሱ የቆዳ ፋብሪካዎች መካከል አብዛኞቹ ችግሩን መቋቋም አቅቷቸው ከገበያው መውጣታቸው የዘርፉን ችግር አመላካች ነው፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ከውጭ የመጡ ኢንቨስተሮች እሴት በመጨመርና የቴክኖሎጂ ሽግግር በመፍጠር የተሻለ ምርት ያመርታሉ ተብሎ ሲጠበቅ ከኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች ያልተሻለ ቴክኖሎጂ በማምጣት ያልተገባ ውድድር ውስጥ ገብተዋል፡፡ በተጨማሪም ከሌሎች ሀገራት ቆዳ እያመጡ በመጠቀማቸው የኢትዮጵያ ብራንድ እየወደቀ መጥቷል፡፡ ነገር ግን የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ሊዳብር የሚችለው በራሱ ባለሀብት፣ ባለሙያና ሠራተኛ መሥራት ሲችል መሆኑን ገልጸው፤ የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ያላቸውን ክፍተት በመሙላት ዘርፉን ማሻሻል እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ቀደም እንደ ወታደር ጫማዎች፣ ቦርሳና ሌሎችም ምርቶች ከውጭ የሚገቡ የነበረ ቢሆንም በአሁን ወቅት ምርቶቹን በሀገር ውስጥ ለመተካት ጥረቶች መደረጉን በበጎ ያነሱት አቶ ከበደ፤ ይህም ቀጣይነት እንዲኖረውና የበለጠ ውጤት ማስመዝገብ የሚችለው በጥሬ ቆዳ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ሲቻል እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

እንደ ባት ጄንዩን ጎት ስኪን፣ ሰላሌ ሽፕ ስኪን፣ አቢሲንያ ሄር ሽፕ ስኪንና ሌሎችም የኢትዮጵያ ቆዳ ብራንድ በመሆን በዓለም ገበያዎች ይታወቃሉ፡፡ ይህን ዕድል በመጠቀም ከጥሬ ቆዳ አሰባሰብ ጀምሮ እስከ ምርት ድረስ በጥራት ለመሥራት ዘርፉ ባለቤት ሊኖረው ይገባል፡፡ ለዚህም ቀድሞ ከነበረው ልምድ በመውሰድ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በንግድና በሌሎች ቦታዎች ተበታትኖ ያለውን የቆዳና ሌጦ ዘርፍ ወደ አንድ ማምጣት ጠቃሚ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ጥሬ ቆዳና ሌጦ አቅራቢዎች ማኅበር ጸሀፊ አቶ መስፍን ለገሰ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ ከ30 በላይ የቆዳ ፋብሪካዎች አሉ ቢባልም በስራ ላይ ያሉት ከስድስት የማይበልጡ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ ቆዳ በየመንገዱና ቱቦ ውስጥ ተጥሎ እየባከነ እንዳለም ያነሳሉ።

እንደ አቶ መስፍን ገለጻ፤ በአነስተኛና ጥቃቅን የተደራጁ ማኅበራት የቆዳ እጥረት እንዳለባቸው በተለያዩ ጊዜያት ያነሳሉ፡፡ ነገር ግን ባላቸው አቅም ምርቶችን አምርተው ለገበያ እያቀረቡ ሲሆን፤ ለውጭም ሆነ ለሀገር ውስጥ ሳይባል ጥራት ያለው ምርት ለገበያ ከቀረበ ምርቱ ተፈላጊ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ከንግድ፣ ከኢንዱስትሪ፣ ከግብርና ሚኒስቴርና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት የተውጣጣ ቡድን በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ተዘዋውሮ በሰራው ጥናት ቄራዎች ቆዳን በየበሩ ጥለው እንደሚሄዱ መረዳት መቻሉን አንስተው፤ በቀላሉ ቢታይ ኬንያ፣ ሱዳንና ሌሎች ሀገራት ተመርቶ የሚሄደው የኢትዮጵያ ምርት እጅጉን ተፈላጊ በመሆኑ መንግስት ከባለድርሻ አካላት ጋር ሆኖ በመስራት የኢትዮጵያ ብራንድ እንዳይበላሽ መጠበቅ አስፈላጊ እንደሆነ ይጠቁማሉ፡፡

# በስለላ ጥበብ የተካኑት የኢትዮጵያ ባለውለታ !

## ባሻ አውአሎም

**ክብረአብ በላቸው**

የካቲት በአትዮጵያ ታሪክ ጉልህ ሥፍራ አለው፡፡ የአትዮጵያውያን የነፃነት ተጋድሎ ታሪክ በደምና አጥንት የተፃፈበት ወር ነው፤ ከእነዚህ አበይት የታሪክ ክስተቶች አንዱ የዓድዋ ድል ነው፡፡ የዓድዋ ድል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ክብር ማኅተም፤ የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተጋድሎ ቀንዲል ነው፡፡ የመላው ዓለም ተፈጥሯዊ ግብር እና ሰብአዊ ክብር የታደሰው፤ በእውነት በፍትህ እና ኀልውና ላይ የተቃጣው ጥቃት ድባቅ የተመታው በዓድዋ የጥቁር ሕዝቦች ታላቅ ድል ነው፡፡

ኢትዮጵያውያን በአድዋ ጦርነት በጣሊያን ላይ የተቀዳጁት ድል መላው አፈሪካውያን ከነጭ ቅኝ ተገዥነትና ከባርነት መውጣት እንደሚችሉ በተግባር ያረጋገጠ ምሳሌ በመኾን ያገለገለ የነጻነት ደወል ነው፡፡ በአፍሪካውያን የጦርነት ታሪክ ውስጥ ከተከበሩና ከተደነቁ ጦርነቶች መካከል አንዱ ኢትዮጵያውያን አውሮፓውያንን ድል የነሡበት የአድዋ ጦርነት መኾኑ በታሪክ ይታወቃል።

የካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም በግሩም ስነስርዓት የተደራጀ ግዙፍ የኢትዮጵያ ሠራዊት የማይታሰበውን ፈጽሟል። ወራሪው የጣሊያን ኃይል ላይ ድባቅ በመምታት ድልን ተቀዳጅቷል። ስግብግብነት በተጠናወተው የአውሮፓውያን መስፋፋት፤ ኢትዮጵያ ነጻነቷን በተሳካ መልኩ አስጠብቃለች ሲሉ ያነሳሉ፤ ዝነኛው የታሪክ ፕሮፌሰር ራይሞንድ ዮናስ፡- «የዓድዋ ጦርነት፤ በዘመነ ቅርምት የአፍሪቃ ድል» በተሰኘው መጽሐፋቸው። ሃያ ዘጠኝ ሺህ ፈረሰኞችን ጨምሮ ከመቶ ሺህ እስከ መቶ ሃያ ሺህ የሚገመት አንድ ሺህ ኪሎ ሜትር በባዶ እግሩ የተጓዘ የኢትዮጵያ የገበሬ ሠራዊት፤ በወታደራዊ አካዳሚ የሠለጠነውን የአውሮፓ ወራሪ ጦር የካቲት 23 ማለዳ አሥራ አንድ ሰዓት ግድም ገጥሞ ከረፋዱ አራት ሰዓት ላይ ማሸነፉን አረጋግጧል ይለናል የታሪክ ተመራማሪው ጆርጅ በርክሌይ፡፡

የዓድዋ ጦርነትና ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ በተሰኘና ዳኘው ኃይለሥላሴ ወደ አማርኛ በተረጐሙት መጽሐፍ ላይ፤ የኢትዮጵያ ገበሬ ሠራዊት ፈረሱ ላይ ሆኖ የጋሻውን እምብርት መሬት ላይ እያጠቀሰ ጐራዴውን አየር ውስጥ እየቀዘፈ በተቆጣና በቆረጠ መንፈሥ በጀግንነት ተዋግቷል፡፡ ጦርነቱ በተጀመረ ከአምስት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሃምሣ ስድስቱም የኢጣሊያ መድፎች ሙሉ ለሙሉ ተማርከዋል፡፡ የቅኝ ገዢውን ወራሪ ሠራዊት ከመሩት ጀኔራሎች ጄኔራል አልቤርቶኒ ሲማረክ የሠራዊቱ ዋና አዛዥ ጄኔራል ባራቴሪ ከጥቂት አጃቢዎቹና በሽንፈት ከተበታተኑ የጣሊያን ወታደሮች ጋር ሸሽቷል፡፡

በዚህ ድብልቅልቅ ያለ ውጊያ ከሃምሣ ስድስቱ የጣሊያን መድፎች በተጨማሪ ብዙ ሺህ ቀላልና ከባድ መትረየሶች እንዲሁም የነፍስ ወከፍ ጠመንጃዎች በአሥር ሺዎችና በመቶ ሺዎች ከሚቆጠሩ መሰል ጥይቶቻቸው ጋር ተማርከዋል፡፡ በአጠቃላይ ምርኮው ወደ አዲስ አበባ የተጓጓዘው በአምስት መቶ አጋሰሶች ተጭኖ ነው፡፡ ታላቁ የጥቁር ሕዝቦች ድል የዓድዋ ድል በመላው ዓለም ፖለቲካ ላይ ከፍተኛና ዋነኛ ለውጦች አምጥቷል፡፡

የእንግሊዝ ጋዜጦች በዓድዋ ድል ማግስት የዓለም ታሪክ ተገለበጠ ታላቅ የትውልድ ኃይል በአፍሪካ ተቀሰቀሰ ... ብለው ፃፉ፡፡ ዘመናዊት ኢትዮጵያን የፈጠሩ የተባሉት ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በአካል ባልተገኙበት የነፃነት ተጋድሎ መሪዎች ጉባኤ የአፍሪካ ብሎም የመላው ዓለም ጥቁር ሕዝቦች የነፃነት ተጋድሎ መሪ ተደርገው ተመርጠዋል።

በዚህ ለነፃነት፣ ለፍትህና ለእኩልነት በተደረገው ተጋድሎ ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ጦሩን እያስተባበሩ መርተዋል፡፡ በቀጥታ በጦርነቱ ከመሳተፍ በተጨማሪ በተለያየ መስክ በመሰማራት ለድሉ መገኘት ጉልህ አስተዋጽኦ ያደረጉ ኢትዮጵያንም አሉ። ከእነዚህ ጀግኖች መካከል በስለላ ጥበባቸው የተካኑት ባሻ አውአሎም በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ።

የመስኩ ሰዎች የጠላትን ጦር እንዳያገግም አድርጎ ድባቅ ለመምታት የስለላ ጥበብ ከሁሉ የላቀ ሳይንስ እንደሆነ ይናገራሉ። ይሄንን ጠንቅቀው የሚያውቁት ጥቁሩ ንጉሥ ምኒልክ ከጣሊያን ጋር ጦርነት ላለማድረግ በዲፕሎማሲ የተቻላቸውን ሁሉ ቢያደርጉም ጦርነቱ እንደማይቀር ሲረዱ፤ ከዘመቻና የጦር መሳሪያ ዝግጅት ጎን ለጎን እሳት የላሱ ሰላዮችንም ማፈላለግ ላይ አተኩረው እንደነበር ይነገራል። በዚህም አሰሳ በራስ መንገሻ አማካኝነት የተገኘው የሐማሴኑ ተወላጅ ባሻይ አውኣሎም አንዱ ነበሩ።

ባሻ በዐፄ ምኒልክና አማካሪዎቻቸው እንደተመከረው ሆነና ለጣሊያኖች ያደረ መስሎ ... ስለ ዐፄ ምኒሊክ ጦር፣ ስለ አደረጃጀቱ ደካማነት እውነት አስመስሎ ማውራት ሲጀምር፤ ጀኔራል ባራቴሪ እውነተኛ ሰላይ ያገኘ መስሎት ሙሉ በሙሉ እምነቱን ጣለበት። እናም ባሻይ የሚናገረውን ሁሉ ማድረግ እንደሚገባው ይወስናል።

ባሻም "... ዐፄ ምኒልክ ጦራቸው በርሃብና በውሃ ጥም ስለተጎዳ በድጋሚ አዋጅ እስኪነገር ወደየቤታቸው እንዲመለሱ አዝዋልና ከጥቂት ወታደሮች ጋር ብቻቸውን በአድዋ ስለሚገኙ በቀላሉ ትይዟቸዋላችሁ....." ሲል ለባራቴሪ ይነግረዋል።

ባራቴሪም ጉዳዩን በማመን ጦሩን አሰልፎ ያለምንም ማመንታት አነጋግሮ ወደ አድዋ ሲገሰግስ...ሳያስበው የሐበሻ የጦር ቀለበት ውስጥ ይገባል!! እነሆ በስንት ዝግጅትና ስልጠና ባሕር አቋርጦ የመጣው ዘመናዊ ጦር በነባሻይ የተቀነባበረ ሴራ በግማሽ ቀን ብቻ የጦር ውሎ እንዳይሆኑ ሆኖ ቅስሙ ተሰበረ!


የታሪክ መዛግብት ባሻ አውአሎም ከጦርነቱ አስቀድሞ ከጣሊያን ጦር ጋር እንዲሰሩ ሆን ተብሎ ተመልምለው የተላኩ የአርነት አርበኛ ናቸው ይላቸዋል፡፡ ከጣሊያን ጋር አብረው፤ ለጣሊያን አድረው፤ ጣሊያንን ሰልለው እንዲመጡ በትዕዛዝ የተላኩ፤ የታዘዙትንም በቁርጠኝነት የፈፀሙ አርበኛ መሆናቸውን ታሪክ ይዘክርላቸዋል፡፡

በየካቲት ወር 1888 ብዙ ቀን በመፋጠጥ ጊዜው ካለፈ በኋላ ዐፄ ምኒልክና ሹማምንቶቻቸው የኢጣልያ ጦር ልብ አግኝቶ ምሽጉን ለቆ ወደ ውጭ እንዲወጣላቸው በበኩላቸው ልዩ ልዩ የመሳቢያና የማታለያ ወሬ ይፈጥሩ ጀመር ከዚህም አንደኛው የኢትዮጵያ ወታደር ስንቅ አልቆበት ለዘረፋ በያገሩ ተበታትኗል ይበልጡም ወደየአገሩ ገብቷል እነ ራስ እከሌም ሞተዋል ወይም ከድተዋል፤ ዐፄ ምኒልክም ታመዋል፤ እያሉ አውቀው ያስወሩ ጀመር በአንድ ወገን ደግሞ እነ ንጉስ ተክለ ሃይማኖት፣ እነ ራስ መኮንን፣ እነ ራስ ሚካኤል ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር እየተማከሩ ጦርነት ብትጀምሩ ዞረን ወደናንተ እንገባለን እያሉ ቢቸግራቸው ለጣልያኑ አዛዥ ደብዳቤ ይፅፉ ነበር።

ጀነራል ባራቲዬሪ የመጨረሻ ውሳኔ ለመወሰን (ከኢትዮጵያ) ሰፈር ያሉት ሰላዮቻችን የሚያመጡልኝን ከሰማሁ በኋላ አንድ ውሳኔ እቆርጣለሁ ብሎ ሲጠባበቅ የእንትጮው ተወላጅ ባሻ አውአሎም መጡና ከላይ ያለውን ሀሳብ ማለትም የኢትዮጵያ ጦር እንደተበታተነ ነገሩት።

ታሪክ እንደሚነግረን በተለይ ባሻ አውአሎም ጣሊያኖች ባልፈለጉት ጊዜ እና ሁኔታ ወደጦርነት እንዲገቡ በማድረግ የተሳካ ስራ ሰርተዋል፡፡ በእርሳቸው የስለላ ጥናት መሰረት የኢትዮጵያ ተዋጊዎች የጦርነት ብልጫ ማግኘት እንዲችሉ አስተዋፅኦ አድርገዋል ይላሉ። እነሆ የካቲት 22 ቀን 1888 ዓም ለሊት ባሻ አውአሎም ከአሉላ አባነጋ ጦር የተቀላቀሉበት- ለሊቱን ሙሉ ብርቱ ጦርነት የተደረገበት – በነጋታው የአድዋ ድል የጥቁሮች ሁሉ ድል መሆኑ የተበሰረበት ቀን ነው፡፡

ከጠላት ሰፈር ያሉት ሰላዮቻችን የሚያመጡልኝን ከሰማሁ በኋላ አንድ ውሳኔ እሰጣለሁ ባለው መሠረት የሰላዮችን ወሬ ከሰማ በኋላ የሰላዮችን ቃል አምኖ የኢጣልያንና የኢትዮጵያን ዕድል የሚወሰንበትን ትልቁን የዓድዋ ጦርነት ለማድረግ የካቲት 22 ማታ ጦሩን አሰልፎ ከምሽግ ወጣ፡፡ አንደኛ ጀነራል ዳቦርሜዳ ከነ ወታደሩ 18 መድፍ ይዞ በቀኝ በኩል ተሠለፈ፡፡ በሌላ በኩል ጀነራል አሪሞንዲ ከነ ወታደሩ 12 መድፍ ይዞ ሠፈረ፡፡ በመካከል ጀኔራል አልቤርቶ ከነ ወታደሩ 14 መድፍ ይዞ በግራ በኩል ሲሰለፍ፤ ጀነራል ኤሌና ከነ ወታደሩ 12 መድፍ ይዞ ከኋላ ደግሞ ጀነራል ባራቲዬሪ 6 የማገ፦ር አሚሊዮ ጦር ይዞ ተንቀሳቀሰ፡፡ ሁሉም በሰሜን በኩል በየ ጦር ግንባሩ ከፊት ሆኖ በታላቅ ጥንቃቄ ከምሽግ ወጥቶ ድንገተኛ



**በእርሳቸው የስለላ ጥናት መሰረት የኢትዮጵያ ተዋጊዎች የጦርነት ብልጫ ማግኘት እንዲችሉ አስተዋፅኦ አድርገዋል ይላሉ**

ጥቃት ለማድረስ ወደ ፊት ገሰገሰ።

እያንዳንዱ ወታደር 112 ጥይት የሁለት ቀን ስንቅ ከላይ የሚደርበውን ካባ የውኃ ኮዳና የዳቦ መያዣውን ይዞ የእርድ ከብት ከነ መሳሪያው ከሠራዊቱ ኋላ ሆነው ስልከኞችና ቴሌግራም አስተላላፊዎች መሣሪያዎቻቸውን ይዘው አንዱ ሰራዊት ከሌላኛው ርቆ እንዳይሄድና ተነጥሎ በመገሥገስ ከጠላት ጦር ጋር ብቻውን ገጥሞ አደጋ እንዳይደርስበት ጥብቅ ትዕዛዝ ተሰጥቶት የመንገድ መሳሳትም እንዳይኖር ተጠንቶ የተዘጋጀ የካርታ ፕላን ይዘው በአገር ተወላጆች ባላገሮች ጭምር መንገድ እየተመሩ ለመጋጠም ገሰገሱ፡፡

በአካባቢ በሜዳ ላይ ተበታትነው የሚታዩ ብዙ ጉብታዎች ስላሉ በእነዚህ ጉብታዎች ላይ ሆነው ቴሌግራፍ ኦፕቲክ በሚባል መሣሪያ እየተመለከቱ ለእከሌ ረዳት ጦር ይጨመርለት እከሌ ወደፊት ይግፋ ወይም ወደኋላ አፈግፍጎ ለእከሌ ይደረብና ይህን ስፍራ ይያዝ የሚል ትዕዛዝ እየተሰጠው ጦርነት ተጀመረ።

ተዋጊ የጦር አባል ቢሞት ወይም ቆስሎ ከወደቀ በቶሎ እንዲነሳና የሕክምና እርዳታ የሚያደርጉ ሁሉ ተመድቦላቸው እንደዚሁም ወሬው ለኢትዮጵያ ጦር ደርሶ ተጠንቅቆ እንዳይጠብቁ በማለት ከሰፈር የመነሻውን ጊዜና ሰዓት ለማንም እንዳይነገር በጥብቅ ታዞ በታላቅ ጉጉት ወደፊት ገሰገሱ፡፡ ነገር ግን ይህ ሁሉ ከኢትዮጵያ ባላሥልጣኖች ጆሮ ያመለጠ አልነበረም።

የኢንቲጮ ተወላጅ የሆኑት ባሻ አውአሎም ሐረጎት፤ የካቲት 22 ቀን 1888 ከጣሊያን ጦር ጋር ወደ አድዋ እየተጓዙ ነበር፡- ያውም የጣሊያንን ጦር እየመሩ፡፡ የካቲት 22 ቀን ለሊት ለየካቲት 23 አጥቢያ በጄኔራል ባራቴሪ የሚታዘዘው የጣሊያን ጦር በባሻ አውአሎም መንገድ መሪነት ከአድዋ ተራሮች ፊት ለፊት ተፋጠጠ፡፡

ይኼን ጊዜ ባሻ አውአሎም በድንገት ከጣሊያን ጦር መሃል አፈትልከው ወደ ኢትዮጵያውያን ገበሬ ተዋጊዎች ምሽግ ገሰገሱ፡፡ ጄኔራል ባራቴሪ ከጉያው አፈትለከው ወደ ኢትዮጵያውያን ጦር የሚሮጡትን ባሻ አውአሎምን አያቸው፡፡ እና ጮክ ብሎ ጠራቸው፡፡

"ባሻ አውአሎም! ባሻ አውአሎም!"

ባሻ አውአሎም ሩጫቸውን ሳይገቱ ጥቂት ዘወር ብለው እንዲህ አሉት፡-

**"ዛሬ አንተን አያድርገኝ!"**

እናም ዘለው ጀግኖቹ ኢትዮጵያውያንን ጦረኞች ተቀላቀሉ፡፡

የአድዋ ድል ሲነሳ የባሻ አውዓሎምን ድርሻ አለማስታወስ ትልቅ ስህተት ነው፡፡ እኚህ ጀግና በስለላ የተጫወቱት ሚና አንድ ጀግና አርበኛ ተኩሶ በመግደል ካደረገው ድርሻ ከፍ ቢል እንጂ የሚያንስ እንዳልሆነ ብዙዎች ይመሰክራሉ። ከድል በኋላ ባሻይ "... በዚያ በየካቲት 22/1888 ዓ.ም ሌሊት፣ የጠላትን ሰራዊት ይገፎ ስገሰግስ አድሬ ንጋት ላይ የካቲት 23 1888 ዓ.ም በዐፄ ምኒልክ እቅፍ ውስጥ አስተኛሁት!" ሲል ቃሉን ሰጥቷል።

ባሻይ የጠላትን ጦር በተሳሳተ መረጃ ማደናገር ብቻ ሳይሆን ጠላትን እየመራ ካደረሰ በኋላም ከወገኖቹ ጎን በመሰለፍ ተዋግቶ አንድ ነጭ እንደማረከም ይነገራል። በዚህ ስራው ባሻይ ከድል በኋላ በንጉሡ እንደተወደሰና በራስ መንገሻ ስር ሆኖ የወረዳ አስተዳዳሪነት ሹመት እንደሰጡትም ተጽፏል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ረቡዕ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የኦሮሚያ ትምህርት ቤቶች ውድድር በባቱ እየተካሄደ ነው

ቦጋለ አበበ

የኦሮሚያ ትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር ካለፈው እሁድ ጀምሮ በባቱ ከተማ እየተካሄደ ይገኛል። ለተከታታይ አስር ቀናት በሚካሄደው በዚህ ውድድር ላይ ከመላው ኦሮሚያ የተውጣጡ ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች እየተሳተፉ ይገኛሉ።

ይህ የትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር በክልል ደረጃ ሲካሄድ ዘንድሮ ለአምስተኛ ጊዜ ሲሆን በበርካታ የስፖርት አይነቶች ፉክክር እንደሚያስተናግድ ተጠቁሟል።



ውድድሩ በጠንካራ ፉክክሮች ታጅቦ ቀጥሏል፣

የትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር በክልሉ ረጅም ዓመት ያስቆጠረ ቢሆንም ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ ባለፉት ስድስት ዓመታት በተለያዩ ምክንያቶች ተቋርጦ ቆይቷል። ዘንድሮ ይህ ውድድር በአዲስ መልክ ዳግም መካሄድ እንደጀመረ የኦሮሚያ ክልል የስፖርት ቢሮ ኃላፊ ዶክተር ቶላ በሪሶ በውድድሩ መክፈቻ ስነስርዓት ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር ገልፀዋል።

ውድድሩ በትምህርት ቤቶች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጠናከርና የትምህርት ቤቶችን ስፖርት ለማሳደግ እንደሚካሄድ የተናገሩት ዶክተር ቶላ፣ በዚህም ክልሉን በአገር አቀፍ ውድድሮች ከመወከል ባለፈ አገርን በታላላቅ የስፖርት መድረኮች የሚያስጠሩ ጠንካራ ስፖርተኞች ማፍራትን ዓላማው እንዳደረገ አስረድተዋል።

ኦሊምፒክን ጨምሮ በተለያዩ ታላላቅ ዓለም አቀፍ የስፖርት መድረኮች ውጤታማ ያደረጉ በርካታ አትሌቶች መፍለቂያቸው ትምህርት ቤቶች መሆናቸውን ያስታወሱት ዶክተር ቶላ፣ የትምህርት ቤቶች ስፖርትን አጠናክሮ ለማስቀጠል ቢሮው ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ እንደሚገኝ ገልፀዋል። የኦሮሚያ ክልል በአፍሪካ ደረጃ በሚካሄዱ የትምህርት ቤቶች የስፖርት ውድድር ኢትዮጵያን ወክሎ ጥሩ ውጤት ማስመዝገቡን በማስታወስም ይህን ለማስቀጠል በትኩረት እንደሚሰራ ጠቁመዋል።

የኦሮሚያ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ ማቲዎስ ሰቦቃ በበኩላቸው፣ አገራችን የበርካታ ወጣቶች አገር መሆኗን ጠቁመው ትምህርት ቤቶች ወጣቶች እውቀት ብቻ የሚሸምቱባቸው ሳይሆኑ ጠንካራ ስፖርተኞች የሚፈሩባቸው ጭምር መሆናቸውን ተናግረዋል። አክለውም በትምህርት ቤቶች ስፖርት ተጠናክሮ መቀጠሉ ለጤናማ አካልና ለብሩህ አእምሮ ጉልህ አስተዋፅኦ የሚያበረክት በመሆኑ ወጣቶች በትምህርታቸው ጠንክረው እንዲወጡ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት አብራርተዋል።

በኦሮሚያ ክልል በምክትል ፕሬዘዳንትነት ማእረግ የማህበራዊ ዘርፍ ክላስተር አስተባባሪ አቶ አብዱልሀኪም ሙሉ፣ የትምህርት ቤቶች ስፖርት መጎልበት አንድነት፣ ወዳጅነትና አብሮ መኖርን ለማጠናከር ትልቅ ፋይዳ እንዳለው ተናግረዋል። እንደ ኦሮሚያ ክልል በትምህርት ቤቶች ስፖርትን በማጠናከር አገርን በታላላቅ ውድድሮች የሚወክሉ ጠንካራ ስፖርተኞችን ለማፍራት የክልሉ መንግስት ትኩረት ሰጥቶ እየሰራበት እንደሚገኝ ገልፀዋል።

የውድድሩ አስተናጋጅ የሆነችው የባቱ ከተማ ከንቲባ አመዲን ኢስማኤል በበኩላቸው፣ ለዓመታት ተቋርጦ የቆየውን የትምህርት ቤቶች ውድድር ዘንድሮ እንደ አዲስ መጀመሩ እንደ አገር ለትምህርት ቤቶችም ጥቅሙ ብዙ መሆኑን አንስተዋል።

የውድድሩ ባለቤት በዋናነት የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ሲሆን የክልሉ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በተባባሪነት የቴክኒክ ድጋፎችን ይሰጣል። ከውድድሩ መጀመር አስቀድሞ የክልሉ ትምህርት ቢሮ ለጋዜጠኞች ባደረገው ገለፃ፣ የውድድሩ ዓላማ በዋናነት ሁሉም ትምህርት ቤቶች ስፖርት ላይ ትኩረት አድርገው እንዲሰሩ ለማነቃቃት መሆኑ ተጠቁሟል። ከዚህ ባሻገር የክልሉን ስፖርት ለማነቃቃትና ለማጠናከር እንደሚረዳም ታምኖበታል።

ከክልሉ ባሻገር ወደፊት ኢትዮጵያን በተለያዩ የዓለም መድረኮች የሚያስጠሩ ጠንካራ ስፖርተኞች መፍለቂያቸው ትምህርት ቤቶች እንደሆኑ በማመን የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ ተጠቁሟል። ኢትዮጵያ ከአትሌቲክስ ስፖርት በስተቀር በሌሎች ስፖርቶች እንደ አፍሪካም እንደ ዓለምም ተፎካካሪ መሆን እየቻለች አይደለም። ይህን ለመለወጥ የአገሪቱ ስፖርት ተስፋ ያለው በትምህርት ቤቶች ውስጥ መሆኑ ተገልጿል።

ውድድሩ በአስተናጋጁ ባቱ ከተማ እና በአርሲ ዞን መካከል በተደረገ የእግር ኳስ የመክፈቻ ጨዋታ የተጀመረ ሲሆን በአትሌቲክስ የወንዶች አንድ ሺ አምስት መቶ ሜትር ፉክክርም ተከናውኗል።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ